# ትግላችን




ጥር – መጋቢት 1962

ቁጥር 2

# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

አዘጋጅ፦ ሃይሌ ፊዳ
c/o P. O. BOX 3198
10364 Stockholm 3
SWEDEN

ጥር – መጋቢት 1962 ዋጋው፦ 1 ብር
ቁጥር 2

ይዘት

| | ገጽ |
|---|---|
| ርዕስ አንቀጽ | 1 |
| ያንኪዎች ፈውዳሉን መንግሥት ሊገላብጡ ነው እንዴ? | |
| የመንግሥቱን ጋዜጣ ስናገላብጥ | 10 |
| ሀ. ሀሊና ቢሱ ብርሃኑ ጥበቡና ትገሳችን | 10 |
| ለ. ብርሃኑ ጥበቡ በገራችን ትምህርት ያልተስፋፋበትን ምክንያት ሲናገር አንስማው | 17 |
| አቅዱን አንድናውቅ | 20 |
| ከአዲስ አበባ አንባቢዎቻችን አንዱ የላከው ጽሑፍ | |
| ከአገር ቤት የደረሱን ዜናዎች | 37 |
| ሀ. የወዝ አደሩ መታጎሪያ ወህኒ ቤት | 37 |
| ለ. የነደጃች አሉላ መታሠር | 46 |
| የታህሣሡ 19ና 20 ያስከተለው ሬቮሉሽናዊ ደያ | 48 |
| ሀ. በገር ቤት የተወሰዱት የተቃውሞ እርምጃዎች | 49 |
| ለ. በአሜሪካ የተከናወኑ የማጋለጫ ትግሎች | 58 |
| ሐ. በአውሮፓ የተደረጉት የማጋለጫ ትግሎች | 58 |
| መ. የማጊል ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር የላካቸው ቴሌግራም | 61 |

ርዕሰ—አንቀጽ

## ያንኪዎች ፈውዳሉን መንግሥት ሊገላብጡ ነው እንዴ?

ያሜሪካን ሞኖፖሎች ወኪል፣ሮጀርስ፣አፍሪካን በሚዞርበት ጊዜ ረቡዕ የካቲት 4፣1962 አዲስ አበባ ደርሶ እንደነበር ይታወሳል፡፡ካፍሪካ አገሮች ሁሉ ኢትዮጵያ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ዋና የጅ አዙር ቅኝና የጦር ሰፈር መሆኗ ሲታወስና ባለፈው ዓመት፣በሀምሌ ወር፣የፊውዳሉ መንግሥት መሪ ዋሽንግተን ሔዶ ባዶ እጁን መመለሱ ሲታወቅ ያሁኑ የሮጀርስ ጉብኝት አያስደንቅም፡፡

አዲስ አበባ በደረሰበት ጊዜ በዩኒቨርሲቲውና በከተማው ትምህርት ቤቶች መዘጋት ምክንያት ግንባር ቀደሞቹ ተማሪዎች በመበታተናቸው፣እንዲሁም እንደተለመደው የጆሮ ጠቢውና የፖሊሱ ጋጋታ መጠን የሌለው በመሆኑ ይህ የያንኪ ሞኖፖሎች ወኪል በቀኒስ ያገኘውንና የሚገባውን የነፍስ ገዳይ አቀባበል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያገኝ ቀርቷል፡፡የሆነ ሆኖ አውሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት ከዚህ ከበላይ ጠባቂዎቹ ወኪል "ጉብኝት" ምን አተረፈ?

ይህ ጽሑፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ የሮጀርስንና የኢትዮጵያን መንግሥት 'ኦፊሲየል' መግለጫ አላገኘንም፡፡አውጥተውም እንደሁ አናውቅም፡፡ቢሆንም የምዕራብ ያጋዜጣ ወኪሎች ባስተላለፉአቸው ዜናዎች ዋናውን ቁም ነገር በሚገባ ጠቅሰውታል፡፡ለምሳሌ የፈረንሣዩ 'አዠንስ ፍራንስ ፕረስ' ሐሙስ የካቲት 5 ቀን ባስተላለፈው ዜና እንዲህ ይላል፣

"ሚስተር ሮጀርስ ሐሙስ ከንጉሠ ነገሥት ኃይለሥላሴና ከጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ጋር ስለአፍሪካ ፕሮብሌሞች ተወያይቷል፡፡ኃይለሥላሴና አክሊሉ የኮሙኒዝም ወደአፍሪካ መግባት በነርሱ አስተያየት ለኢትዮጵያ የሚያሰጋ መሆኑን ገለጹለት፡፡

ነገር ግን ሚስተር ሮጀርስ ያስተናጋጆችን ስጋት የተካፈ

ሰው አይመስልም፡፡ደግሞም የጦር መሣሪያን መስጠት ሳፍሪካ
የፖለቲካ ፕሮብሌሞች መፍትሔ መስሎ እንዳልታየው በይገል
ጽሳቸው አልቀረም፡፡"

በጭፍና በቀላል አማርኛ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መሣሪያ ከ
መከልከልም አልፎ የኢትዮጵያን ፊውዳል መንግሥት አኮርዶታል
የሮጀርስ አነጋገር ኃይለሥላሴንና አክሊሉን በጥፊ እንደመም
ታት ሊቆጠር ይችሳል፡፡እስቲ ጉዳዩን ጠጋ ብለን እንመልከተ
ው፡፡

ፊውዳሉ መንግሥት "ኮሙኒዝም" በሚለው ማጭበርበሪያ ቃል አ
ያስፈራራ ዕርዳታ ማግኘትን የተማረው ከራሱ ከአሜሪካን ኢም
ፔሪያሊዝም ነው፡፡አሁን የኮሙኒዝምን ስጋት ያነሰው የበሳይ
ጠባቂውን አስደንግጦ ችግር ያነበበውን የኢትዮጵያ ሕዝብ —
በተለይ የባሌን፣የኤርትራን፣የጎጃምን፣የኦጋዴንን — የሚጨፈ
ጭፍበትንና መቀለል በጀመረ የሥልጣን አልጋው ሳይ ተወዝፎ
የሚቆይበትን መሣሪያ ለመጠየቅ ነው፡፡የኢትዮጵያ መንግሥት
ኮሙኒስት የሚለው ዘረፋና ጭቆና እንገፍግፎት የተነሳውን ገ
በሬ፣በየፋብሪካው ሥራ እያቆመ ለአለት ጉርሱ እንኳ የማትበ
ቃ ደመወዙን ለማስጨመርና ኢምንት የሆነች የሰው ልጅ መብቶ
ን ለማስጠበቅ የሚታገለውን ሠራተኛና፣ባገር፡ቤትም ሆነ በው
ጭ አገር የሚቷቷመውንና የሚያጋልጠውን ተማሪ ነው፡፡

ያሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶችም ኮሙኒስት የሚሉት ልክ እንደዚሁ
ያለውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡አሜሪካኖች ማንኛውንም ቅ
ኝ አገዛዛቸውን የሚቃወም ብሔራዊና ሕዝባዊ የነፃነት እንቅ
ስቃሴ ሁሉ ኮሙኒስት እንደሚሉት ዓለም በሙሉ ያውቀዋል፡፡አ
ጼ ሃይሬው የኢትዮጵያ መንግሥት የኮሙኒዝምን ስጋት ለያንኪዎች
መጥቀሱ ሌባን ሌባ ቢሰርቀው እንዴት ይደነቀው የሚባለውን
የአበቶች ተረት ያስታውሰል፡፡

የሆነ ሆኖ ፊውዳሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ከበርሚል ሙሉ ፈን



ጂ ሳይ መቀመጡንና ብሔራዊ የሆነ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በአገ
ሩ ውስጥ በመሩፋም ሳይ መሆኑን ከንጉሠ ነገሥቱና ከአክሊሉ
ይበልጥ ያንኪዎች ያውቁታል፡፡ታዲያ የተጠየቁትን መሣሪያ ለ
ምን ከለከሉ?

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ዋና ጥረት በኢትዮጵያ ውስጥ የ
ጀመሩትን ዘረፋ በመጠኑም ሆነ በዓይነቱ ለማስፋፋት ሲሆን
ይህንኑ ከግቡ ለማድረስ በማታለያ የብሔራዊ ሽሽ የተሸፈነ
ሥልጡን አሽከር ያስፈልጋቸዋል፡፡ያሁኑ አገዛዝ በቋሚም ሆነ
በሠራሩ የበሰበሰ በመሆኑ ትዕዛዛቸውን በሚገባ ከሥራ ሳይ
ለማዋል ብያዓግተው አልቀረም፡፡በዘመናዊ በስም ብቻ የዘመና
ዊነት ለምዱ ተሸፋፍኖ አንዳንዱ ጥቃቅን ያስተዳደር ለውጦች
ን ያደረገ በመምሰል ሊፈነዳ የቀረበውን የኢትዮጵያን የሬቮ
ሉሽን በምብ በጊዜ የሚያከሽፍላቸው መንግሥት ያስፈልጋቸዋል
የትሳልቅ ፊውዳል ባላባቶች ጥቅም ጠባቂ የሆነው የኃይለሥላ
ሴ መንግሥት ይህንን ሊያደርግላቸው አልቻለም፡፡

ስለዚህ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ለኃይለሥላሴ መንግሥት መ
ሣሪያ አለመስጠታቸው አያስደንቀንም፡፡እንዲያውም ካለፈው ዓ
መት ጀምረው የሚያውርዱት የጋዜጣ ዘመቻ የሚያመለክተው ይህ
ን መፈረረስ የጀመረና የጃጀ አጼም ገልብጠው በፈንታው በበ
ለጠ ሊያገለግላቸው የሚችል ሌላ አሸንጉሊት መንግሥት ሊተኩ
ማቀዳቸውን ነው፡፡

ከነዚህ ጋዜጦች ጥቂቶችን በመምረጥ ኢምፔሪያሊስት ዓለም ዶ
ሮ" ታላቅ መሪ፣አርቆ አስተዋይ፣ሕዝቡን ወደሃያኛው ክ
ፍለ ዘመን ያሸጋገረ መሪ ..." እያለ ሲያወድስ የነበረ
ውን ዘረ እንዴት ለውጦ ማቃለል እንደጀመረ እንይ፣

ባለፈው ሀምሌ ወር ነሐሴ ወደዋሽንግተን ሲጓዝ "ኒውስዊክ"[1]
የተባለው የታወቀ ያሜሪካን ምናፖሎች ጋዜጣ ሲጽፍ "38 ዓ
መት ሙሉ ስይደፈር ኢትዮጵያን የገዛው ኃይለሥላሴ አገሪቱን

---

[1] ቅጅ [illegible] ሁሉ ይሰጣል

ወደሃያኛው ክፍለ ዘመን ለማሸጋገር ያለውን ምኞት ደጋግሞ ተናግሯል፡፡ በርግጥም ወደዚያ ግብ ትንሽ እርምጃ አድርጓል፡፡ ነገር ግን ኃይለሥላሴ ገና ብዙ መንገድ መራመድ እንዳለበት ለመገንዘብ ኢትዮጵያን ሳጭር ጊዜ መጎብኘት ይበቃል" ይላል ጋዜጣው ራሱ አፄሃይሌ በመሆኑ ፊውዳሉ የኢትዮጵያ አገዛዝ በፍጥረቱ ከመናገር አልፎ የዚህን ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ የማይችል፣መወገድ ያለበት ሥርዓት መሆኑን አይናገርም፡፡ ይሁንናም ስለፓርላማ ምርጫ — የመራጮችን ምልክት — እንስቶ "ወጣም ወረደም ማንኛውንም ውሳኔ የሚያደርገው ንጉሡ መሆኑን" ከስታወስ በኋላ የሚቀጥለውን ጽፎአል፡፡

"... ጠለቅ ብለው ሲመለከቱ፣በዚህ፣ከአፍሪካ አገሮች ሁሉ የረዘመ የነፃነት ታሪክ ባለው አገር ብዙ ብልሹ ነገር አለ፡፡ በማዕዱን ሀብትና በእርሻ በኩል ኢትዮጵያ ከሁሉ በላይ ሀብታም ከሆኑት ያፍሪካ አገሮች መካከል ናት፡፡ ነገር ግን ተራው ኢትዮጵያዊ፣በተለይም ከአዲስ አበባ ውጭ ያለው፣የሚኖረው ኑሮ በዓለም ከሁሉ የተቀረደ ነው..."

የኢኮኖሚዋን መበላሸት፣የፖለቲካ ችግሮችን፣የትምህርትንና የዩኒቨርሲቲው፣ፕሮብሌሞች ይዘረዝርና ንጉሡ የማንንም ሒስ እንደማይቀበል ይጠቅሳል፡፡ ቀጠል ያደርግና የኢትዮጵያዊያን ምኞት አስመስሎ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች በማዘጋጀት ላይ ያሉትን ተንኮል እንዲህ ሲል ይዘረዝራል፡፡

"አንዳንዱ ያዲስ አበባ ሊበራሎች ተስፋቸውን የሚጥሉት ዕድሜው 52 ዓመት በሆነውና ምናልባትም በቀጥታ መስመር የንጉሡ ነገሥቱን አልጋ በሚወርሰው በኃይለሥላሴ ልጅ፣በአስፋ ወሰን፣ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንዱ ሊበራል አስተያየቶች ቢኖሩትም አልጋ ወራሹ በርግጥ የሚታወቅ ሰው አይደለም፡፡ ያረጀው ንጉሥ ከወደቀ አልጋወራሹን ለስሙ አስቀምጦ እርገጠኛ ስልጣኑን የሚወርሰው ጦር ሠራዊት ባይሆን አይቀርም፡፡ አንዳንዱ ኢትዮጵያዊያን የዚህ ዓይነቱን ለውጥ በጉጉት ይጠባበቃሉ..."



ባጭሩ፣ አገራችንን የሚገዟት አሜሪካኖች በልጋ ወራሹ ይህን ያህልም እምነት የላቸውም፡፡ ደግሞም ለወደፊቱ ከበዱልን አገዛዝ አንዱ የወታደር መንግሥት መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መስመሮች በያዘው ገጽ "ኒውስዊክ" ንጉሡንና አልጋወራሹን ከግራና ከቀኝ አድርጎ፣በመካከላቸው አንድ ዱሀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያሳይ ፎቶግራፍ ካስቀመጠ በኋላ ከጎርጊው "ያልተፈጸመ ተስፋ፣ከ38 ዓመታት አገዛዝ በኋላ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያን ዘመናዊ ለማድረግ አልቻሉም፡፡ አንዳንዱ ሊበራሎች ተስፋቸውን የሚጥሉት በልጋወራሹ በአስፋ ወሰን ነው" ሲል ይደመድማል፡፡

"ሉስአንጀለስ ታይምስ"[2] የተባለው የሞኖፖሎች ጋዜጣም ባለፈው ዓመት የተፈጸመውን የኢትዮጵያ ወጣቶች ትግል ምክንያት በማድረግ ይህንኑ የመሰለ አስተያየት ይሰነዝራል፡፡ እስቲ እሚለውን እንስማ፡፡

"ኢትዮጵያ የትምህርት ድርጅት አላት፡፡ ነገር ግን በአፍሪካ ከሁሉ ከተበላሹት ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ነው፣ የትምህርት ዕድሜ ካላቸው ህጻናት ውስጥ በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙት ቁጥር ከኢትዮጵያ የሚያንሰው በናይጀርና በሶማሊያ ሪፓብሊክ ብቻ ነው፡፡ ከብሔራዊ ገቢዋ ከሁሉም አገር ያነሰውን ገንዘብ ለትምህርት የምታውል ያፍሪካ አገር ኢትዮጵያ ናት፡፡ በሌላም በኩል ስታቲስቲኩ እንደዚሁ አሰቃቂ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ለመቶ ሺህ ሕዝብ አንዱ ሀኪም ብቻ ነው ያለው፡፡ ይህም ከአፍሪካ የመጨረሻው ቦታ ነው...

"ንጉስ ነገሥቱ ሁልጊዜ ስለእድገት ያወራል፡፡ ነገር ግን የተማረው ወጣት ትውልድ ምንም የተጨበጠ ውጤት አ

ሳየም፡፡ንጉሠ ነገሥቱ የመሬት ድልድል ሚኒስቴር አቋ
ቋሞአል፡፡ነገር ግን የመሬት ድልድል አልተደረገም፡፡
ንጉሠ ነገሥቱ የልማትና የፕላን ዲሬክተር ሾሞአል፡፡
ነገር ግን ወጣቱ ተቃዋሚ ትውልዱ ያየው ፕላን ወይም
ልማት የለም...
ይልና ጥቂት ቀዝቃዞች የሚመኙት የገበሬ ሪፎርምን መሆኑን
ጠቅሶ፡አሳይ ኒውስዊክ እንዳለው ሁሉ፡የኢትዮጵያ ተማሪዎ
ች የሚፈልጉት የወታደር ኩ ዴታ ነው ሲል ይደመድማል፡፡

ኢምፔሪያሊስት ዓለም ስለኢትዮጵያ ፊውዳል አገዛዝና ስለመ
ሪዎቹ አስተያየቱን እንደለወጠ በሚገባ የሚያሳይ ምናልባት
'ሰንዴይ ታይምስ መጋዚን'[3] የተባለው የእንግሊዝ ሞኖፖሎች
ጋዜጣ ባለፈው ሰኔ ያወጣው ጽሑፍ ባይሆን አይቀርም፡፡ይህ
አዱሃሪነቱ የታወቀለት መጽሔት የንጉሡን ፎቶግራፍ በቀለም
ከሽፋኑ ላይ አውጥቶ "አንበሰው ቆጂ" በሚል አርእስት
ስር ከጻፈው የሚከተሉትን መስመሮች እንጠቅሳለን፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ወደፊት የምትራመድ
ትመስል ነበር፡፡የባዕድ ኩባንያዎች በዚህ ፀጥ ባለና
እንግዳ ተቀባይ በሆነ አገር ኢንቬስት ለማድረግ የሚ
ጓጉ ይመስል ነበር፡፡ለመመሳሰሸ፡ለቴክኖሎጂ ማሠልጠኛ
ለኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያና ለትምህርት ብዙ ዕርዳ
ታ ተሰጠ፡፡አዲስ በተፈጠረው ፓርላማ ሕዝቡ ተስፋ አ
ሳድሮ ነበር፡፡ከአራት ዓመት በፊት ኢትዮጵያ የወዳጅ
ነትና የሰላም አገር ትመስል ነበር፡፡አሁን ግን በጣ
ም የተበላሸ ነገር አለ፡፡

"ያገሪቱ ኢኮኖሚ ወደኋላ የተመለሰ ይመስላል፡፡የቡና
ዋጋ በጣም ዝቅ ባለበት በሁኑ ወቅት ቡና ወደውጭ ከ
ሚላከው ሸቀጥ 60 በመቶ ነው፡፡... እንዱስትሪ ከ
ብሔራዊ ገቢ 3 በመቶ ቢሆን ይህችም እንኳን አሁን
ዝቅ ብላለች፡፡



"ከተሰጠው ዕርዳታ ይበልጡ ተሰርቋል፡፡ወይም ባክኗል፡
አሁንም ቢሆን ቡና ወደሚያፈሩት የደቡብ ምዕራብ ኢት
ዮጵያ ክፍሎች የሚያደርሱ ጥሩ መንገዶች የሉም፡፡በብ
ዙ መቶ የሚቆጠሩ የውጭ አስተማሪዎች ቢኖሩም ከሕዝቡ
መሐይምን ያልሆነ 5 በመቶ ብቻ ነው፡፡
ሁኔታ
"የራቡ ያዲስ አበበለበይበልጥ የሚያነገበግብ ሆኗል፡፡
የለማኞች፡የሌቦች፡የቤት አዳሪዎችና ያቃጣሪዎች፡የብል
ግና ፎቶግራፍ ሻጮች ጋጋታ ባያጋጥም በመንገዱ ለመሄ
ዱ አይቻልም፡፡

"የኢኮኖሚው ኃይል አሁንም የተያዘው በበላገሩ ላይ ፊ
ውዳል ሥልጣኑን በሰፈሩት ራሶች ወይም ባላባቶች ነው
... ንጉሠ ነገሥቱ፡እንደማነኛውም የመካከለኛ ዘመን
የእንግሊዝ ንጉሥ፡ፀጥታ የሚሰማው ባላባቶች እዚያው ቤ
ተ መንግሥት ዙሪያ ሆነው ከሱ ያልራቁ እንደሆነ ነው"

ከዚህ ቀጥሎ ስለፓርላማው ከንቱነት፡በባለፈው ዓመት የተማ
ሪዎች ትግል፡እያደገ ስለሚሔደው ፀረአሜሪካን ስሜት፡ስለን
ዳንዱ ምሁራን ሥጋት፡ስለነገዶችና ስለኤርትራ ግንባር ይጠ
ቅስና ለተለመደው "ከኃይለሥላሴ በኋላስ?" ለሚለው ጥያቄ
መልስ "ምናልባት አልጋውን ቢወርስ የማይቀረው አልጋወራ
ሽ አገሪቱን በአንድነት ለመያዝ የሚችል ሰው አይደለም" ይ
ላል፡፡በመጨረሻም ወደፊት በኢትዮጵያ በኮንጎ፡በቢያፍራና
በሱዳን ከደረሰው ሁሉ የበለጠ የርስ በርስ ጦርነት ሳይነ
ሳ እንደማይቀርና የኢትዮጵያ 'ሮማንስ' ከፍጻሜ እንደሚደ
ርስ ይተነብያል፡፡ይህ እንኳን የእንግሊዝ ሞኖፖሎችን ምኞት
የሚገልጽ እንጂ መሠረት የሌለው ትንቢት ቢሆንም ኢምፔሪያ
ሊስቶች — በተለይ ያሜሪካን — የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊውዳሉ
ን ሥርዓት ለመገልበጥ ባንድነት የተነሳ ዕለት "የርስ በ
ርስ ፍጅት" በሚል ማታለያ አመካኝተው በሠሬያ ኃይል ጣ
ልቃ መግባታቸው እንደማይቀር የሚያሳይ መሆኑን እናስታውስ

ጊዜና ቦታ አጥሮ ነው እንጂ ባለፈው ዓመት ጀምሮ ኢምፔሪ
ያሊስቶች ስለፊውዳሉ የኢትዮጵያ አገዛዝ መቶ በመቶ አስበ
ቸውን እንደለወጡ ከብዙ ጋዜጦች ጠቅሰን ለማስየት በቻልን
ነበር፡፡ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መሣሪያ አልሰጥ ብሎ የኃ
ይለሥላሴን መንግሥት መሰልቦ ያበፈረውና አሁንም ሮጀርስ
ለኢትዮጵያና ላፍሪካ ሕዝብ ያዘነ ይመስል "መሣሪያ መስጠ
ት ፖለቲካዊ ፕሮብሌሞችን አይፈታም" ያለው ይህንኑ ያመለ
ክታል፡፡ቁም ነገሩ የት ላይ ነው?

ኢምፔሪያሊስት አገሮች የጋዜጣ ዘመቻቸውን በሰፊው የጀመሩ
ት የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጋድሎ ፊውዳሉን ሥርዓት ከነሥረ መ
ሠረቱ ባናጋበት ወቅት ነው፡፡አሁን በገሬችን ያለው ሥርዓ
ት ቀኑ የተቆጠረ መሆኑን አሳይ አንዳልነው ሁሉም ተገንዝ
ቦታል፡፡እንግዲህ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ምርጫ ከሁለት
አንዱ ነው፡፡

1 የኃይለሥላሴን መንግሥት ገልብጦ የሚስማማውንና ሥል
ጡን አገልጋይ የሚሆነውን ወታደራዊም ሆነ ሌላ ሥል
ጣን ቶሎ በገሪቷ ላይ ማስፈርና በገሪቷ ለውጥ የተ
ደረገ በማስመሰል ጥቅሙን በቀላሉ ማስፋፋት

2 የኃይለሥላሴ መንግሥት፣በፈለጉት መንገድ ሊያገለግላ
ቸው እንደማይችል እያወቁ፣የሚጠይቁትን ዕርዳታ ሁሉ
— መሣሪያ፣ገንዘብ ... — በመስጠት አሁን ከወደቀ
በት የችግር ማጥ እንዲወጣ ለማድረግ መሞከር

ከዚህ በላይ ያሰስነው የጋዜጦች ዘመቻ የሚያመለክተው ያን
ኪዎች የመጀመሪያውን ምርጫ እንዳደረጉ ነው፡፡

ለማንኛውም ነገር ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቪየትናም ተወ
ጥሮ በተያዘበት ባሁኑ ወቅት፣በጠቅላላው በእስያ በፍሪካና
በደቡብ አሜሪካ ያሉት ብሔረዊ የነፃነት ተጋድሎዎች ተፋፍ
መው ከሁሉም ወገን በጠቀበት ባሁኑ ወቅት፣ከሀያ ሚሊዮን



በላይ የሚሆኑት ወንዶቻችን አፍሮ አሜሪካዊያን ኢምፔሪያ
ሊዝምን ከምሽጉ ውስጥ ሆነው በሚያራውጡበት ባሁኑ ወቅት፣
ባጭሩ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በኢኮኖሚና በፊናንስ፣በፖለ
ቲካና በሚሊቴር፣በውስጥና በውጭ ችግሮች ተተብትቦ በሚገኝ
በት ባሁኑ ሰዓት የተለመደውን ዕርዳታ — የራሱ ጥቅም በ
በለጠ የሚስፋፋ መሆኑን ባያረጋግጥ — እንዴት አድርጎ በ
ገፍ ለፊውዳሉ ሥርዓት ሊሰጥ ይችላል?

ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ተፈጥሮውን ሊለውጥ አይችልም፡፡ያ
ሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዋና ዓላማ ኢትዮጵያን — እንደሌሎ
ች ተበዝባዥ አገሮች ሁሉ — ጥገኛ በማድረግ ጥሬ ሀብቷን
ና የሕዝቧን የጉልበት ፍሬ ለመዝረፍ፣ያላቂ ሸቀጡ ማራገፊ
ያ ለማድረግ ቢሆን ይህንኑ ምኞት ከግቡ ለማድረስ በማታለ
ል፣በተንኮልና በሽንገላ፣ደግሞም ይህ ካላዋጣው በመሣሪያና
በጉልበት እየተጠቀመ የሕዝቦችን የነፃነት ተጋድሎ ለማኮሸ
ፍና ለመደምሰስ፣ጭቆናውንና ብዝበዛውን ለዘላለም ለማኖር
መፍጨርጨሩ አይቀርም፡፡ፊውዳሉን የኢትዮጵያ መንግሥት መሣ
ሪያ ቢከለክል ይህንኑ የራሱን ፀረረቮሉሽናዊ ጥቅም ለመጠ
በቅ እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዝኖ አለመሆኑን ስለምናውቅ
በዚህ አንታለልም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የያንኪዎችንና የገብረ አበሮቻቸ
ውን ተንኮል ሁሉ አከሽፎ ድልን እንደሚጎናጸፍ አ
ንጠራጠርም፡፡

---

[1] Newsweek, July 14, 1969

[2] Los Angeles Times Magazine, June 1, 1969

[3] The Sunday Times Magazine, June 8, 1969

## የመንግሥቱን ጋዜጣ ስናገላብጥ

### ሀ.ሀቢና ቢሱ ብርሃኑ ጥበቡና "ትግላችን"

ብርሃኑ ጥበቡ የተባለው የያንኪዎች አሽከር፣ጥር 14፡1962 በወጣው 'የኢትዮጵያ ሔራልድ' በሚባለውና 'ያሜሪካን ሔራልድ' ተብሎ መጠራት በሚገባው የጉመን መጠቀሳያ ወረቀታቸው 'ትግላችንን' በማንቋሸሽ ጽፎአል፡፡በተሸጠች ምላሱ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተሰለፈበትን ዓላማ ዘልፎአል፡፡መቆጠብን በማያውቅ የጥራዝ ነጠቆች ድፍረት የኢትዮጵያን ወጣት ትውልድ ስም ብቻ ሳይሆን እንደማርክስና ሌኒን ያሉትን ትልልቅ ሰዎች ለማታለል ሞክሮአል፡፡ከዕለት ወደዕለት እንደብረት እየጠነከረ የሚሔደውን ፀረበሳበትና ፀረኢምፔሪያሊስት አቋማችንን በማሸሞአጠጥ ሲያልፈው ቃጥቶአል፡፡

ባለፈው የትግላችን ቁጥር — መስከረም—ታህሣሥ — እንዳመለከትነው ብርሃኑ ጥበቡ ፋሽስቱ የኢትዮጵያ መንግሥት በኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ የበለጠ አመፅን እንዲፈጽም በጥብቅ "ካሳሰቡት" ጋዜጠኞች ውስጥ ቀንደኛው ነው፡፡ብርሃኑ ጥበቡ የወደፊት እርምጃ ጠር፣የወደኋላ ጎታቹ የኢትዮጵያ መንግሥትና ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ቡችላ መሆኑን በጽሑፎቹ ደጋግሞ አስመስክሮአል፡፡

ባለፈው የትግላችን ቁጥር እንዳመለከትነው ከብርሃኑ ጥበቡና ከመሰሎቹ አዱር ባዮች ጋር ለመከራከር አንሻም፡፡ነገርግን እነዚህን ወገናቸውን ቁልጭ አርገው የመረጡትን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ማጋለጥና ተንኮላቸውን ማክሸፍ ሊታለፍ የማይገባው ተግባር ነው፡፡ብርሃኑ ጥበቡና መሰሎቹ አሁን ተመዝግበው አንድ ቀን የክህደታቸውን ዋጋ ከኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ እጅ ይቀበላሉ፡፡



ጥር 14፣1962 የወጣው የጉመን መጠቀሳያ "ሔራልድ" የሚለው ምንድን ነው?

በነሐሴ 1961 የወጣው "ትግላችን" የያዛቸውን የአትማት ስህተቶችና የፊደል ግድፈቶች፣እንዲሁም ከአነጋገር ዘዴ የመጡ የቁጥር ልዩነቶች ይጠቅስና በነዚህ ላይ በመመርኮዝ ትግላችንንና የአውሮፓውን ማኅበራችንን ይሰድባል፡፡ባንዱ ቦታ ሁለት ሺህ ያልነውን በሌላ ቦታ ከአምስት ሺህ የማይበልጥ፣4.5 በመቶ መሆን የነበረበትን 5 በመቶ — አንደኛ ደረጃ በነበረ ጊዜ የተማረውን የነጥብ ዕውቀት ሸጦታል መሰል? —፣ባንዱ ገጽ 35 ብር ያልነውን በሌላ ቦታ ወደ አምሳ ብር ገፍቶ ... በማለታችን "እዚህና ውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አገራቸውን በትክክል እንደያውቁ መጠየቅ ይበዛባቸዋል" ቢል ይወሸክታል፡፡አቡ ማሸሙቀጠጡ ያለው ነው፣በዕውነቱ ከሆነ የገለጠው በሚያነበበት ጊዜ ታሳትን ከመመልከት አልፎ አስቦ እንደማይመለከትና እንደማይከተል ነው፡፡

ሔስ — ክሬቲክ — ሲባል እንደነብርሃኑ ጥበቡ ያሉትን ጥራዝ ነጠቆች የሚያስደስታቸው የዚህ ዓይነቱን ጥቃቅን ግድፈትና የአነጋገር ዘዴ ሲያስከትል የሚችለውን ልዩ ልዩ ትርጉም ፈልጎ መልቀም ሆኖ ነው እንጂ አዙሮ ለሚያስብ ሰው በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ያሉት ተማሪዎች ቁጥር ሁለት ሺህ ሆነ አምስት ሺህ፣በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ካለባቸው የኢትዮጵያ ወጣቶች በትምህርት ላይ የሚገኙት 4.5 በመቶ ሆኑ 5 በመቶ ወይስ 15 በመቶ፣የመሃይምኖች ቁጥር 95 በመቶ ሆነ ወይስ 98 በመቶ፣የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ያመት ገቢ 35 ብር ሆነ 50 ... የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዓለም ሕዝቦች ሁሉ የደኸየና የተበዘበዘ ነው ያልነውን አይለውጠውም፡፡አሁን በኢትዮጵያ የሰፈረው አገዛዝ ጊዜው ያለፈበት ፊውዳል ሥርዓት መሆኑንና ከሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጋር

ተማጥኖ ዕድሜውን የሚያራዝም መሆኑን፣ ይህ ሥርዓተ መንግሥ
ትና የበላይ ጠባቂው ያሚሪካን ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ
ሕዝብ ተደምስሰው የሚጠፉበት ቀን የተቃረበ መሆኑን አይለ
ውጠውም።

ብርሃኑ ጥበቡ የሚዘልፈው የትግላችን ቁጥር በርከት ያሉ
መሠረታዊ ጉዳዮችን ይዟል። "መሬት ላራሹ" የተባለው የኢ
ትዮጵያን ሕዝብ ልባዊ ምኞት የሚገልጸው ረቮሉሽናዊ መዝሙ
ር አለበት። ርዕስ አንቀጹ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች
ማኅበር ዘጠነኛ ጉባዔ ያደረጋቸውን ኢትዮጵያ ነክ ጥናቶች
ከጠቀሰ በኋላ የኢትዮጵያ ገበሬ፣ ሠራተኛና ተማሪ መሠረታዊ
ለውጥን በአገራችን ለማምጣት መከተል የሚያስፈልጋቸውን ጉዳ
ና ያመለክታል። ከርዕስ አንቀጹ ቀጥሎ ያለው ጽሑፍ በሚሪ
ካን ያሉት ጓደኞቻችን ማንኛውንም ችግርና መሥዋዕትነት በይ
ፋ የፊውዳሉ መንግሥት መሪ ኃይለሥላሴ እንደተለመደው
ያሚሪካን ኢምፔሪያሊዝምን መሪዎች ምጽዋት ለመለመን በሔደ
ጊዜ በቆራጥነት ረቮሉሽናዊ ዕርምጃ ወስደው ኃይለሥላሴንና
ያሚሪካንን ኢምፔሪያሊዝም እንዳሸበሯቸው በሰፊው ይገልጻል

አፃን፣ የተባለው የትግላችን ቁጥር ብዙ ቁም ነገሮችን አዘ
ሏል። በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በረቮሉሽናዊ
ቅርጊቱ የወደፊት ተራማጆችን — የስዊድን ሕዝብ ጭምር —
አድናቆት፣ ድጋፍና ወዳጅነት እንዳተረፈ የሚያስቁ ጽሑፎችን
ይዟል። ደግሞ በትምህርት በኩል የ12ኛ ክፍልን ፈተና ቀ
ተቀበሉት 3552 ወጣቶች ውስጥ ለከፍተኛ ትምህርት የታጨ
ት 738 — ማለት 20.8በመቶ ብቻ — መሆናቸውን የሚገልጽ
ጽሑፍ አለበት። ቡረታ የገቡ ወታደሮች 'አቤት' ቢሉ እንደ
ተደበደቡ የሚያመለክት ጽሑፍ፣ ስለዓለም በታኝ፣ ስለታኘው የ
ያንኪዎች የስለላ ጣቢያ፣ ስለአደላ የሚናገር ገጽ፣ በኢትዮጵ
ያ በሰነገሠው ፊውዳል ፋሽስት አገዛዝ የሚያስረዳ ድርሰት
... አለበት።



እነዚህን ሁሉ የማይከዱ ዕውነቶችና ቁም ነገሮች ጠቅሶ በ
መከራከር ፈንታ ብርሃኑ ጥበቡ የተማሪዎች ሥራ "የሰው ስ
ደብና "ወሮ በላነት" ነው ብሎ ተሰድቦ ለማለፍ ይሞክራል፣
ይህ ሁሉ ማንን ለመደለል ነው? አገሩን ወዳጅና ቀን ኢትዮ
ጵያዊ ሁሉ ትግላችንን አንብቦ መጽሔቱ የቆመበት መሠረት
የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም መሆኑንና የያዛቸውም ጽሑ
ፎች የማይከዱ ዕውነቶች መሆናቸውን መገንዘብ አይሳነውም፣
ደግሞም ብርሃኑ ጥበቡና መሰሎቹ ትግላችንን ለማንቋሸሽ የ
ተነሱት መጽሔታችን — እንደታገለ — በሰፊው ሕዝብ ዘን
ዱ ተደማጭነት ስላተረፈ መሆኑን አንረሳም። ይህም የሚያበ
ረታታ ነው።

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ከሉንድ እስከማልሞ
ባደረገው ፊውዳሉን መንግሥት የሚያጋልጥ ሠልፍ ላይ ብዙ በ
ረቮሉሽናዊ ምንባብ የተጻፉ በሌዳዎችን ይዞ ነበር። ከነዚ
ህም ውስጥ ዋናዎችን ለመጥቀስ ያህል፦

— ጠላቶቻችን ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ናቸው፣ ትግላ
ችን ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ነው።

— የኢትዮጵያን ሕዝብ ተጋድሎ ደግፉ።

— መሬት ላራሹ።

— ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ። ሕዝባዊ ዴሞክ
ራሲ ይኑር።

የሚሉ ነበሩ። እነዚህ በሌዳዎች በመጽሔቱ ውስጥ በታተሙት
የበልፉ ፎቶግራፎች ውስጥ በግልጽ ይታያሉ። ከነዚህ ውስጥ
ብርሃኑ ጥበቡ አንዱንም አይጠቅስም። እርሱን የከነከነው
— ለምን እንደሆነ መገመት ይቻላል እንጂ በግልጽ አይታወ
ቅም — "የስዊድን ኢምፔሪያሊዝም ይውደቅ" የሚለው በሌዳ
ቢሆን ርዕስ አንቀጹንም "የስዊድን ኢምፔሪያሊዝም" ብሎታ
ል።

ከሁሉ አስቀድመን አንዱ ነገር በማጤራት የብርሃኑ ቀበቡን የጃብ ችኮልነት እናባይ፡፡"የስዊድን ኢምፔሪያሊዝም" ይውደቅ የሚለውን በሌላ የሠሩትና ይዘውት ከኢትዮጵያዊያን ጓደኞቻቸው ጋር የተሰለፉት የስዊድን የወደፊት ራማጁ ዶርጆቻች አበሳት ናቸው፡፡

በብርሃኑ ቀበቡ ርዕስ አንቀጽ ውስጥ ከከንቱ ዝባዝንኬ አልፎ መሠረታዊ ቶም ነገርን የሚመለከት አበበ በናር ስለ 'ስዊድን ኢምፔሪያሊዝም' በመጠቀሙ ተናዶ በሚደነፋበት ጊዜ ስለኢምፔሪያሊዝም ጠቅላላ መልክ ቢያወራ የበነዘራቸው ሦስቱ የመጨረሻ አንቀጾች ነበሩ፡፡

እዚህ ላይ ቶም ብለን ስለኢምፔሪያሊዝም በሰፊው ለማውሳትና ብርሃኑን በተደበለቀ አስተያየቱ ለመመለስ ብንሞክር በተደሰትን ነበር፡፡ ነገር ግን ከበነዘራቸው አንዳንዱ አበበች እንደምናየው ብርሃኑ የኢምፔሪያሊዝምን አጻጻፍ — መቸም የቱ ነገር አጻጻፍ(spelling)እሬት መደብ ሞቱ ናቸው በደንብ አጥንቶ እንደሆነ ነው እንጂ ስለኢምፔሪያሊዝም ይዘት ምንም እንደማያውቅ ተረድተናል፡፡ሌላው ቀርቶ ኢምፔሪያሊዝምን ዓይነተኛ የሚያደርጉትን ዋና ዋና ጠባዮች እንኳን የተረዳ አይመስለንም፡፡ስለዚህ በዚህ አበበ ላይ ከሱ ጋር መዳረቅ ስንዴን በጭንጫ ላይ መዝራት ስለሚሆንብን ለጊዜው እንለፈውና ስለኢምፔሪያሊዝም ለማውራት በሚያዝበት ጊዜ ስለነበቻቸው አንዳንዱ አበቦች እናውስ፡፡

ብርሃኑ ቀበቡ ያሜሪካን ጊቶችን ለማስደሰት የበጡን የቶውን አያወረደ ሲቀበጥር ባይወዱ የያንኪዎችን ተንኮል እንደሚዘረዝር እናስተውል፡፡

ስዊዲኖች በውጭ አገር "የሰላሳ ጊደች የሷቸውም፣በጋዜጠኛ አስመስለው ያገር ቶስጂቦች አይልኩም፣ወደፊት ተራማጅ መንግሥትን ለመደምሰስ በወታደርና በታንክ አነስተኛ ጉረቤት



አገርን ፈጽሞ ወርረው አያውቁም፣በበሕር ማዶ ገዘት የላቸውም፣በዘር ልዩነት አይጠቀሙም..." ይላል፡፡በዚህ አነጋገሩ ብርሃኑ ቀበቡ የሚፈልገው ስም በይጠሬ ሶቪየት ኅብረትን ወቅቦ ከያንኪዎች ጊቶች አይዞህ በርታንና ጉርሻን፣እንዲሁም የተሻለ ወንበር ለማሞቅ የመመረጥ ዕድልን ለማግኘት ነው፡፡

እረ ለመሆኑ በነዚህና ከዚህም በበቡ ተንኮሎች የቆኙ አገዛዝን በዓለም ላይ ለማስፈር በከንቱ የሚፍጨረጨረው ማነው የኩባንና የሰንቶ ዶሚንጎን፣በጠቅላላው የላቲን አሜሪካን የኮንጎን፣የጋናንና የሌሎችን አፍሪካ አገሮችን፣የቬየትናምን፣የታይላንድንና የላኦስን፣የኢንዶኔዥያንና ሌሎችንም የእስያ አገሮችን...እናንሳ፡፡እናቶ ብንሔዱ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች በጋዜጠኛ፣በሰብሳባና በበርታ ካገኙ፣በበተዳጀርና በወታደር፣በከንቱ ነገር ከማበሪ አያሰሙበሉ አገራችንን ከዳር እስከዳር በበሰይ ቀልተዋት የለምን? ያሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች በነመንግሥቱ ነዋይ የተቀሰቀሰውን 'ኩዴታ' በውርቫሳን ኃይል አከሸፈውት የለምን?ያሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ለአፍሪካ ሕዝብ ነፃነትና ለዓለም ሰላም ጠንቅ የሆነውን የሰሰሳ የጦር ሰፈር በቶቀደበቹ ምዱሬችን ላይ ተክለው ይጨፍሩብን የለምን? ለዘር ልዩነት የሆነ እንደሆነ ከሃያ ሚሊዮን በላይ የሆኑትን አፍሮ አሜሪካዊያን በፋሽስት ጭቆና ሥር የሚያኖሯት ያሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች በሰመራና በዲስ አበባ፣በጋዝ አገራችን፣ኢትዮጵያዊ —ብርሃኑ ቀበቡ ጭምር — የማይገበቡትን መሸታ ቤቶች አቁመው የለምን?እፃን፣ከፍ ነገው አርቆ ማየት የማይችለው ብርሃኑ ቀበቡ ባይወዱ የጊቶችን ተንኮል በመጠኑም ቢሆን ዘርዝሯል፡፡

በጽሑፉ መጨረሻ ቢያሸማጥጥ "የሰፊው ሕዝብ ሕጋዊ መሪዎች እንዲሆን ተፈጥረናል ብለው በጭፍረት የሚናገሩት እነዚህ ምሁሮች ወደአገራቸው ተመልሰው ቦታቸውን የሚይዙበትን ቀን በጉጉት እንጠብቃለን" ይላል፡፡በአውሮፓ የኢት. ተማ.ማኅ.

ተማሪ የሰፊው ሕዝብ መሪ ነው፣ወይንም ለመሆን ይፈልጋል፣ ወይንም መሆን አለበት ብሎ የተናገረበት ወቅት የለም።ወደፊትም አይኖርም።በኢምፔሪያሊስቶች ፕሮፓጋንዳና ጉርሻ አይናችን የታወረው ብርሃኑ ጥበቡ አሳይ ብሎ ነው እንጂ — ምናልባት እንደተለመደው የሰቀሰውን ልክ መሆንና አለመሆን ለመወሰን ቢፍጨረጨር አባቡን ባይቀስም አልፎ ይሆናል የመጽሔታችንን ሽፋን ብቻ አንቧን የተመለከተ ሁሉ ሊገነዘበው እንደሚችለው ዓላማችን እንደቀን ብርሃን የጠራ ነው፣ አርማችን "ተማሪና ምሁር ከገበሬውና ከሠራተኛው ጋር ተዋሀዱ።ከነርሱ ተማር፣መልሰህም አስተምራቸው።አብረህ በመሰለፍ አዲሲቷን ኢትዮጵያ መስርት" ይላል።

የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ከመሸጥ የተረፉት ምሁራን ይህንን መሪ ቃል ከሥራ ላይ ለማዋል ያላቸውን ቁርጥ አሳብ በንደበትም ሆነ በድርጊት ደጋግመው ገልጸዋል።አዲሱ የኢትዮጵያ ትውልድ በርግጥ ከሰፊው ሕዝብ ጋር ተሰልፎ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ከውዷ አገራችን ገጽ የሚያጠፋበት ቀን ደርሷል።ብርሃኑ ጥበቡና መሰሎችም እስከሁን በገራችን ታይቶ የማይታወቅና ከሕግ የወረደ ፀረረቮሉሽናዊ ጥቃቻቸውን ሲይቀጥሉ በዚህ ትውልድ ላይ የሚያፈሱት በዚሁ ምክንያት ነው።

ብርሃኑ ጥበቡና መሰሎቹ ፋሽስቱ መንግሥት በኤርትራ፣በጎጃም፣በባሌና በሩቢ ሕዝብ ላይ ወንጀሉን ቢፈጽም በደስታ ሲያጨበጭቡ መኖራቸው ቢታወቅ አሁን በቅርቡ ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ አመፅ እንዲፈጽም አበረታትተውታል።ይህ አልበቃቸው ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብና የዩኒቨርሲቲ ወንድሞቻችን የደረሰባቸውን ጭፍጨፋና ሥቃይ በውጭ ያሉትም እንዲቃወሙ መንግሥታቸውን በመጎትጎት ላይ መሆናቸው ግልጽ ነው።በወንጀል ላይ ወንጀል ለማየት ይቅነጠነጣሉ።ነገር ግን በውጭ አገር ያለነው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፊውዳሉን አገዛዝና ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን ከነቡችሎቻቸ



ው ከመቃወምና ከማጋለጥ የሚገታን ኃይል ፈጽሞ የለም።ለኢትዮጵያ ሕዝብ በብሔራዊ መብትና ነፃነት ለነታገል ማናኛውንም መሥዋዕትነት ለመቀበል ዝግጁ ነን።እንቅሳሁን ገዛው የከፈቶትን የክበር ጉዳና ለመከተል ዝግጁ ነን።ለዚህም በመስኮብ፣በስቶክሆልምና በፓሪስ፣በኒውዮርክና በሌሎችም ከተሞች የወሰድናቸው እርምጃዎች ምስክሮች ናቸው።

ብርሃኑ ጥበቡና መሰሎቹ ትግላችንን ለማጉደፍና ከግባችን እንዲነገታ ለማሰናከል ትንኮሳቸውን በብዙ ቅጥር፣እንደሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት ጭቆናውን እያበሰው በሔደ ቁጥር አጿማችን የበለጠውን እየጠሩና እየጠነከረ ይሔዳል።ሙሽታችን የበለጠውን በሕዝቡ ዘንዶ እየተሰራጨና ተደማጭነት እያገኘ ይሔዳል።ትግላችን የበለጠውን እየዳበረና እየሰፋ ይሔዳል አቈሰሪውን የኢትዮጵያን መንግሥት፣የበላይ ጠባቂውን ያሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝምንና ቡችሎቻቸውን ደላሮቸውና መሣሪያቸው፣ትንኮሳቸውና ጭካኔያቸው ፈጽሞ ከጥፋት ሊያድናቸው አይችልም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል።

---

## ለ.ብርሃኑ ጥበቡ በገራችን ትምህርት ያልተስፋፋበትን ምክንያት ሲናገር እንሰማው

ጥር 16፣1962 በወጣው "ሔራልዱ" አታሳዋ ብርሃኑ ጥበቡ ስለትምህርት በኢትዮጵያ ሲናገር ትምህርት ያልተስፋፋው አገራችን ደሃ ስለሆነች፣የቢንዚን ማዕዱን ስለሌላት ነው በማለት ሲያጭበረብር ይሟከራል።ከዚህ በታች የተሰጡት ቁጥሮች ከዩኔስኮ የስታቲስቲክስ — UNESCO Statistical Yearbook,1967 — የተቀዱ ናቸው።ለማመሳሰል ያህል

የጥቂቶች ያፍሪካ አገሮችን ቁጥርም ወስደናል። እንጎላ አሁንም በቅኝ ገዛት ስር የሚገኝ ያምስት ሚሊዮን ሕዝብ አገር ነው። የቀሩት አገሮች ነፃ ከወጡ ሃያ ዓመት አልሞላቸውም። እንዲያውም እንደነአልጄሪያ፣ኬንያና ማላዊ ያሉት አሥርም ዓመት አልሞላቸው።

| አገር | ዓ.ም. | 1ኛ ደረጃ | 2ኛ ደረጃ | 2+3 |
|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 |
| አልጄሪያ | 1960 | 28 | 8 | 22 |
| | 1965 | 43 | 11 | 34 |
| እንጎላ | 1960 | 9 | 3 | 7 |
| | 1964 | 16 | 5 | 12 |
| ካሜሩን | 1960 | 57 | 5 | 42 |
| | 1965 | 74 | 14 | 60 |
| ኮንጎ | 1960 | 58 | 7 | 43 |
| ብሬዛቪል | 1965 | 80 | 21 | 66 |
| ኢትዮጵያ | 1960 | 5 | 0.4 | 3 |
| | 1965 | 7 | 2 | 6 |
| ኬንያ | 1960 | 49 | 4 | 35 |
| | 1965 | 52 | 7 | 39 |
| ማላዊ | 1960 | 41 | 1 | 29 |
| | 1966 | 36 | 3 | 26 |
| ሱዳን | 1960 | 11 | 6 | 9 |
| | 1965 | 13 | 7 | 11 |
| ግብጽ | 1960 | 40 | 21 | 35 |
| | 1965 | 46 | 34 | 43 |



"1ኛ ደረጃ" የሚለው ሰንጠረዥ ከ5 እስከ 14 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ወጣቶች ይወስድና ከመቶው ስንቱ ባንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ እንደሚገኙ ያሳያል። "2ኛ ደረጃ" የሚለው ከ15 እስከ 19 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ወስዶ ከመቶው ስንቱ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ እንደሚገኙ ያሳያል። 4ኛው ሠንጠረዥ — የመጨረሻው ሠንጠረዥ — በደፈናው ከ5 እስከ 19 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ወጣቶች ወስዶ ከመቶው ስንቱ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ እንደሚገኙ ያመለክታል።

እነዚህን ቁጥሮች በማመሳሰል አድሃሪው የኢትዮጵያ መንግሥት እንዴት ወደኋላ እንዳስቀረን ለመገንዘብ ይቻላል። አገራችን ድሃ አይደለችም። ሕጻናቷን መቶ በመቶ ለማስተማር፣ ራሱን የቻለ ነፃ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችላት በቂ የተፈጥሮ ሀብት አላት። ወደፊት እንዳንራመድ የሚያደርጉን ፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበርና የበላይ ጠባቂው ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ናቸው።

እነዚህን ቁጥሮች ሲያይ ብርሃኑ ምን ይል ይሆን? <u>በተለመደ ክህደቱ</u> "ምነው የቅኝ ገዛት ብንሆን ኖሮ" ባይል አይቀርም ምናልባት።

## አቋሙን እንዲናውቀ

### ከነዲስ አበባ አንባቢዎቻችን አንዱ የላከው ጽሑፍ

በኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይ የተጫነው ባላባታዊ — ፊውዳላዊ ሥርዓ
ት በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን የአርበታ ኃይሎች በሙሉ አፍኖ ስ
ለያዛቸው በገበርናም ሆነ በሌላ ልዩ ልዩ ሥራ የተሰማራው ሕ
ዝብ — በጠቅላላው ተበዝባዡና ተጨቋኙ ክፍል — በጉልበቱ የ
ሚያፈራው ከድካሙ ጋር የተመጣጠነ አይደለም፡፡ይህንንም ጥሮ
ግሮ የሚያገኘውን አነስተኛ ገቢ አፍኝ የማይሞሉ ተባዮች —
የበዝባዥ መደብ አበሎች — ያለሥራ ተቀምጠው እየገፈፉ ለመጨ
ጻደቂያና ለመፈንጠዝ፣እነርሱን መሰል አገዛዞቻቸውን ለማስተና
ገኛ፣የብዝበዛ ሥርዓታቸውን ለመጠበቂያና ሕዝቡን ለማስፈጃያ
የሚጠቀሙባቸውን ድርጅቶች — የወታደር ኃይልን፣የፖሊስ ኃይል
ን፣ጆሮ ጠቢዎችንና በጠቅላላውም ሕዝብ አወናባጆችን — ለማስ
ፋፊያና ለማጠንከሪያ ስለሚያባክኑት ሰፊው ሕዝብ በችግር ላይ
ችግር እየተከበበ ሔዷል፡፡በየጊዜው እየጨመረ የሚሔደውን የ
ዘመኑን የመቀናጫ ወጭ የተለመደው ባላባታዊ ብዝበዛ የማይመል
ሰው በመሆኑ "አልሚ ነኝ" ባይ ገዥዎቻችን — መዠገሮቻችን
ማለቱ በይበል አይቀርም — ደሃውን ገበሬና ሠራተኛ በልዩ ል
ዩ ዘመናዊ መንገዱ — የገቢ ግብር፣የግብር መዋጮ፣የጤና ታክ
ስ ...— ከልክ በለፈ መጠን ይገፉታል፡፡አለመቻሉን ለማስ
ታወቅ ሌሞሑን ከበጫ በልዩ ልዩ ዘመናዊ መሣሪያ ይፈችታል፡፡

ይህ ቅጥ የለሽ የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓት ገበሬውን በጭፈፉ
ፈንታ ጠብመንጃውን እንዲያነግት አድርጎታል፡፡ሠኸት የሰለቸው
ን ሠራተኛ የሥራ መሣሪያዎችን እንዲሰብር አስገድዶታል፡፡በ
ገበሬውና በሠራተኛው ላይ በየዕለቱ የሚወሰደውን ፋሽስታዊ አ
ርምጃና — ከሥራ ማስወጣት፣ማሰር፣መግደል፣በቦንብና በናፓልም
መደብደብ፣በሕዝቡ መካከል የሚገኙ አነስተኛ ቀራኒዎችን እያሩ
ሩጦ ማበጣበጥ — ለሰው ልጅ መሠረታዊ መብት የሚደረገውን የ



ተቀደሰ ሕዝባዊ ተጋድሎ ሕዝቡ የት ሰምቶ? የወሬ ማሠራጫ
ዎች በሙሉ በመንግሥቱ እጅ በመያዛቸው የገዥዎችን ማታለያ
ፕሮፓጋንዳ ከመለፈፍ በስተቀር ለሕዝቡ ዕውነተኛ ዜና አቅ
ርበው አያውቁም፡፡በጥቂቱም ቢሆን — አቅማቸው በፈቀደው
መጠን — የሕዝቡን ችግር፣ፍላጎትና ስሜት መግለጽ የጀመሩ
ት የተማሪ ማኅበራት መጽሔቶች ብቻ ናቸው፡፡ታዲያ በነዚሁ
ስ ላይ ዕውነቱ ዕውነት ብሎ መነገሩ፣አቋሙ እንዲታወቀ
መሞከሩ ምንን አስከተለ?

እስቲ የሰሞኑን ጋዜጦች እንመርምር፡፡እስቲ የነነጋሽ ገብ
ረማርያምን፣የነከበደ አኒሳን፣የነፍቅሬ ሥላሴን፣ወልደሃናን
የነበርሃኑ ቀበቡን፣የብሔራዊ ስሜት ለፋፊዎቻችንና የበላዩ
ቻቸውን ውሽከታ ጠጋ ብለን እንመርምር፡፡

### አቶ ነጋሽ ገብረማርያምን እንስማው፣

ኅዳር 19፣1962 በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ "ከመ
ጠኑ አለፈ" በሚል ርእስ አንቀጽ ስር አቶ ነጋሽ ገብረማ
ርያም "ገና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ከሚመኙት የኢኮኖሚ
የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ የሥልጣኔ ደረጃ ለመድረስ...
ንብረትና ጸጥታው የተጠበቀ፣መንግሥቱ የጸና አቋም እንዲኖ
ረው አስፈላጊ ነው" ይላል፡፡እዚህ ላይ አቶ ነጋሽን ለመ
ጠየቅ የምንፈልገው፣ ኸረ ለመሆኑ ኢኮኖሚ የሚያድገው፣የፖ
ለቲካ አቋም የሚሻሻለውና ማኅበራዊ ኑሮ የሚያድገው ምን
ጊዜ ነው? መንግሥት ምንድን ነው? መንግሥትስ ፀጥታን የ
ሚያገኘው ምን ጊዜ ነው?የኢትዮጵያስ ኢኮኖሚ ባሁኑ ወቅት
ለማደግ የተሳነው በአርግጥ የፀጥታው አለመጠበቅ አንቀፋት
ሆኖበት ነውን?

የአንዱ አገር ኢኮኖሚ የሚያድገው የአርበታ ኃይሎችና የአ
ርበታ ግንኙነቶች መጣጣም አገኝተው አንዱ ለአንዱ ድጋ
ፍ ለመስጠት የሚችሉበት ማኅበራዊ ሥርዓት ሲኖር ብቻ ነው

ይህም በሌላ አነጋገር ቢቀርብ የአንዱ አገር ኢኮኖሚ የሚ ያድገው

— የእርሻ መሣሪያዎች በለቤትነት

— በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉት መደቦች ቦታና ግንኙነት

— የሀብት አደላደል

የእርሻ ኃይሎች ከደረሱበት ደረጃ ጋር ቢስማሙ ብቻ ነው ማለት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የእርሻ ኃይሎችና የእርሻ ግንኙነቶች ወጋ በሰን እንመልከት።በገጠር ያሉት ዋና ዋና የእርሻ ኃይሎች መሬት፣ጊዜ ያለፈባቸውና እንዳያድጉ የፊውዳሉ ሥርዓት አፍኖ የያዛቸው የማረሻ መሣሪያዎችና ዘዴዎች፣ገበሬዎች... ቢሆኑ በከተማ ደግሞ በተዘበ ሁኔታ$_2$ብቅ ብቅ በማለት ላይ ያሉት ፋብሪካዎችና የንግዱ ሥራዎች... ናቸው።እንግዲህ ባለንበት ዘመን በኢትዮጵያችን የእርሻ ግንኙነቶችን ዓይነተኛ የሚያደርጉት በገጠር የመሬት አያያዝ ሁኔታና በአራሹና በአከራዩ መከከል ያለው ግንኙነት፣በከተማ ደግሞ የንግዱና የኢንዱስትሪ አያያዝ ሁኔታ፣በከበርቴና በሠራተኛ መከከል ያለው ግንኙነት ናቸው ማለት ነው።

በአገራችን ዋናው የእርሻ መሣሪያ፣መሬት፣በጥቂት ሰዎች እጅ ተይዟል።ጪሰኛው አራሽ በዚያው ባለችው መሣሪያ ጥሮ ግሮ የሚያፈራውን እነዚህ ባለርስቶች ይገፉታል።ሳበ አደፉ ገበሬ ለፍቶ ማብላትን እንጂ ለፍቶ መብላትን ከተነፈገ ዓመታት አልፈዋል።

አንዱ ጪሰኛ ከሥራው ፍሬ እስከሦስተኛው ድረስ ሰብ ሳቡ እንዲሰጥ በሕግ እየተገደደ፣እንጨት እየፈለጠና እጥር እያጠረ፣ውሃ እየቀዳና ቤት እየሠራ፣እህል እየፈጨ፣ባለ



ርስቶችን በማገልገል ከሰብአዊነት ወደኢሰብአዊነት ደረጃ ከተለወጠ፣ዓመታት አልፈው ዓመታት ቢተኩ ገፉና ጭቆናው እየበሰበት ከሔደ በጪሰኛውና በባለርስቱ መከከል ምን ዓይነት ፀጥታ ሊኖር ይችላል?

ጪሰኛው አፍርቶ የሚቀጣ ከሆነ የማንን ኢኮኖሚ ለማዳበር ነው የሚጧትነው? በፀጥታ ቀረሀ ገረሀ ሥራ የምትሉት የገዥዎችን የቅንጦት ፍላጎት ለማርካት አይደለምን? ታዲያ ለዚህ ለምን ብሎ ይልፋ? ይኸውልህ፣እቶ ነጋሽ፣የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የገታውና በሰበት ከመርገጥ አልፎ ወደኋላ እንዲዘር ያደረገው እንዲህ ያለው የኢኮኖሚ ግንኙነት ነው።

ሌት ተቀን እንጀቀን አቆፍ መኖር በልችቶች፣የጭቆና ብዛትና በየዕለቱ በኑሮ መኰሳቆል አስመርሮት ቀፈርና ቀንበሩን ጥሎ፣ትዳሩን ፈትቶ ወደከተማ የሸሸውስ የትናንቱ ገበሬ የዛሬው ሠራተኛ ከምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?

በከተማ በሥራ ፍለጋ ከተንቀዋለለ፣የበረንዳ ውርጭ ከደረቀውና የሰው ፊት ከገረፈው በኋላ አነስተኛ ሥራ ያገኘ እንደሆነ በነዱ በኩል የባዕዱ ካፒታሊስቶች የሥራውን ፍሬ ያለርህራሔ ይመጡታል፣በሌላ በኩል የትናንቱ ባለርስት፣ዛሬ በውጭ ካፒታሊስቶች ሥር ተሸሸጉ ንግዱን በማስፋፋት ብዝበዛውን በተራቀቀና መጠን በሌለው መንገዱ የሚያካሔደው ባለርስት ከበርቴ፣ያችኑ አነስተኛ ደመወዙን እንደገና ይዘርፈዋል።በጠላቶቹ እጅ ተመልሶ ከመውደቅም በላይ ሌላ አዲስ በዝበዛ ተጠመረበት ማለት ነው።

አንዱ ሠራተኛ ዋስትና በሌለው የሥራ ሁኔታ ቀንና ሌት እየደከመ በቀን ቢበዛ ከአንዱ ብር በላይ አያገኝም።በከተማ ኑሮ በቀን አንዱ ብር ተገኝቶ፣በዚያችው የቤት ኪራይ ከፍሎ፣ምግብ በልቶ፣አካልን ሸፍኖ... ለመኖር ይቻላልን? ቢቀ የሀብታም፣ከገበሬው ወንድሙ እየተዘረፈ የሚሸጠው እህ

ል የሀብታም፣የኑሮ ዋጋ በየዕለቱ የሚያሻቅብ ታዲያ የሠራተኛው ኑሮ ፊት ከነበረው ምን ተሻለ?

ገበሬውና ሠራተኛው እንደዚህ ባለ በሚያንገፈግፍ ሁኔታ ቢኖሩ፣ከነርሱ በተዘረፈው ሀብት ባለርስቶችና ባለገንዘቦች — በጠቅላላው በዝባዦች የሚመጻደቁ ከሆነ በነዚህ በዝባዥና ተበዝባዥ መደቦች መካከል ምን ዓይነት ፀጥታ ሊኖር ይችላል?አቶ ነጋሽ ፀጥታ ቢል ገበሬውና ወዝአደሩ ተያይዞ የመጣውን በዝበዛ አሜን ብለው መቀበል አለባቸው ማለቱ ነው መሰል?እንደዚህ መናገሩ ለሚጣልለት ፍርፋሪ ዋስትና ለመስጠት ያህል ነው እንጂ በበዝባዥና በተበዝባዥ መካከል ፀጥታ ሊኖር እንደማይችል ያጠፋል ብለን አንገምትም፡፡

መንግሥት ምንድን ነው? እንደአቶ ነጋሽ እንደሚነገረው ከሆነ የአንድን አገር ሕዝብ ጥቅም የሚጠብቅ የበላይ ድርጅት ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ድርጅት በጣት በሚቆጠሩ አገሮች ውስጥ እንደተቋቋመ አንጠራጠርም፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው ክፍለ—ዓለምና በተለይም በአገራችን ያለውን ሁኔታ ብንመለከት ንጉሣታት፣መሣፍንትና መኳንንት፣ባላባቶችና ከበርቴዎች በአንድነት ተጠራቅመው ጥቅማቸውን ለመጠበቂያና የበዝበዛ ሥራቸውን ለማቃለያ ያቋቋሙት ድርጅት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ቀበሮዎች በአንድነት ተሰብስበው የበጎችን ጥቅም ለመጠበቅ ምን ዓይነት ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ?

በኢትዮጵያችን ይህ መንግሥት የተባለው የበዝባዦች ድርጅት የራሱን ጥቅም ለመጠበቅና በዝበዛውንም ሕጋዊ ለማድረግ ከፍትህ የራቀ ሕገ መንግሥት አውጥቶ፣የወታደርና የፖሊስ ኃይሉን አጠንክሮ፣መሠረታዊ የሆነ ሰብአዊ መብቱን የጠየቀን ሁሉ ሲያስርና ሲገድል፣መላውን ሕዝብ ሰላም አሳጥቶ ሲበጠብጥና ሲያበጣብጥ ይገኛል፡፡ ታዲያ እንዲህ ያለውን፣ሕዝብን ለመጨቆኛ የተፈጠረ፣ኃይል እንዴት አድርገን የሕዝብ ጥቅም መጠበቂያ እንለዋለን?



እንደዚህ ዓይነቱ ፀረሕዝብ የሆነ መንግሥት ሊጠና የሚችለው በዝበዛውን በማጠንከርና በወታደራዊ ኃይል በመጠቀም ብቻ ስለሆነ ተበዝባዡ ክፍል የመንግሥቱን መውደቅ እንጂ መጠናት አይፈልግም፡፡የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ እድገትም የሚገኘው ይህ ለብዙ ዓመታት በሕዝቡ ጫንቃ ላይ እንደከባድ ቀንበር ተጭኖ የኖረው መንግሥት ተደምስሶ ወዲያ በርሱ መቃብር ላይ ዕውነተኛውን የገበሬውንና የሠራተኛውን ጥቅም ጠባቂ መንግሥት ሕዝቡ ራሱ ሲመሠርት ብቻ ነው

ቀጥሎ አቶ ነጋሽ "በጥቂት ተማሪዎች አነሳሽነት አልፎ አልፎ ፀጥታ የሚያደፈርስ፣በሕዝብ ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ የሚያደርስ ሁከት" እየተፈጠረ ማስቸገሩን በተለመደው ድብስብስ አነጋገር ይገልጣል፡፡

አቶ ነጋሽ ይህን ዓረፍተ ነገር የወረወረው እንደተለመደው በከባቢያው ያለውን ሁኔታ ሳያስተውልና በአእምሮው ሳያሰስል እንጂ እንደሚገባው በደንብ አስቦበት አይመስልም፡፡በኢትዮጵያ ሕዝብ የትምህርት ዕድል በመነፈጉ እርግጥ የተማሪዎች ቁጥር በጣም ትንሽ ነው፡፡የትምህርት እድሜ ካሳቸው ወደትምህርት ቤት መሄዱ የቻሉት ወደአምስት በመቶ ገደማ ብቻ ሲሆኑ ብዙ ተማሪ ከየት ሊያመጣ ነው? ነገር ግን እነዚያው ያሉት ሙሉ በሙሉ በትግሉ ለመሳተፋቸው በየጊዜው የተነሳው የተማሪዎች እንቅስቃሴ በግልጽ አሳይቷል፡፡በገጠርም ሆነ በከተማ ትምህርት ቤቶች እየተደጋገሙ የተዘጉት ለሰብአዊ መብትና ለፍትህ በሚደረገው ትግል ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች በመሣተፋቸው አይደለምን?ጥላሁን የሞተ እለት በአንድ ጊዜ ከአሥር ሺህ በላይ የሆኑ ተማሪዎች መሰለፋቸው ሁሉም ተማሪ ለመነሳቱ የማያጠራጥር ምስክር አይደለምን? አቶ ነጋሽ፣ሕዝቡን ያነሳሳው አንተ እንደምትለው "ጥቂት ተማሪዎች" ሳይሆኑ የነቀዘው የአገሩ ሁኔታ ነው፡፡

ለመሆኑ በነርሱ ተነሳ የተባለው "ፀጥታ ማደፍረስ" ምንድን

ነው? መሬት ሳራሹ ይሰጥ፣ዱህነት ወንጀል ነወይ?፣ የሰ/
ማዊ ሰልፍ መብት አይነፈግ፣በሕሳችን አይርከስ፣ትምህርት
ለዱሃውም ይዳረስ፣ባህል አንዓፊዎችና ያሜሪካን ሰላዮች ከ
ገራችን ይውጡ፣አገራችን ለአሜሪካን አትሸጥ ... ማለት ፀ
ጥታ ማደፍረስ ነው እንዴ?ፀጥታስ ያደፈረሳችሁ እናንተ፡፡
ስትገርፉ፣ስታስሩና ስትገድሉ በረሃብ አለንጋና በበሽታ
ሕዝቡን ስታስነቁ ፀጥታ አልደፈረስ ይሆንን?

"የተማሪዎች ዓላማ 'በአገሪቱ ውስጥ ብጥብጥ ማንሳት፣አሁ
ን ያለውን ሕገና የመንግሥት አቋም ማፍረስ፣ሃይማኖትን መ
ጻረር፣ ያለውን በሕልና ልማዱ መሸር፣የአገሪቱን የነገዱና
የጉስ አንዱነት አንዓልነበረ ማዱረግ' መሆኑን ከመገለጥ
አልተቆጠቡም" ይላል አቶ ነጋሽ፡፡ይህ የበሰበሰ መንግሥት
ሕዝቡን ለመደለያ የሚያበካውን ወሬ በግልጽ ማስተመጡ ነው
የዱሃን መብት ለመጠበቅ ሲባል ብጥብጥ ቢነሳ፣አለ የሚበለ
ው ፀጥታ ቢደፈርስ፣ለመሳው ሕዝብ ደህንነት ሲባል አሁን
ያለው ሕገና የመንግሥት አቋም ቢፈርስ፣በፊው ሕዝብ ይጠቀ
ማል እንጂ አይጉዳም፡፡ችጋር፣በሽታና መሐይምነት አየተጨ
ወተበት ነፃነቱን ቢጠይቅ የጥይትና የቦንብ ዝናብ አያረገ
ፋበት ምን ፀጥታ አለው? ታዲያ ብጥብጥን ምን አመጣው?መ
ብትን መጠየቅ ብጥብጥ ማንሰት ነውን? ዕውነተኛና ደስታ
የተመሳበት ፀጥታ ይኑር፣ፀረሕዝብ የሆነው መንግሥት በሕዝ
ባዊ መንግሥት ይተካ፣አሁን በአገሪቱ ያለው የነገዶችና የ
ጉባዎች ገንኙነት የገዢው ክፍል እንደመሰለው የሚከበውና
የሚንደው መሆኑ ተር ቶ፣የያንዳንዱ ነገዱና ጉሣ እኩልነት
ተጠብቆ ሕዝቡ ራሱ በሚያደርገው መፈቃቀዱና መተባበር ይተ
ካ ማለት ምን መጥፎ ነገር ታየበት? ሃይማኖትንስ ማን ተ
ጻረረ? ማናቸውም ተማሪ ሆነ ምሁር ሃይማኖትን አይጻረርም
የሃይማኖት እኩልነት ይኑር፣ማናቸውም ሃይማኖት ፖለቲካዊ
ሥልጣን አይሰጠው ብቻ ነው የተባለው፡፡

ከአጻጻፉ እንደተረዳነው አቶ ነጋሽን የአዲስ አበባ መምጫ



ት ያስደነገጠው ይመስላል፡፡የመማር ዋናው ቁቅም ተመራምሮ
ና ጠቃሚ ዕውቀትን ሁሉ ከያለበት ቆስሞ በየቦታው አያስገ
ቡ ለሕብረተሰቡ እንዲያገለግል ለማድረግ ነው፡፡አዲስ አበ
ባ የመጣውም በአና ፈቃዱ በይሆን ከጊዜያዊው የሕዝቡ ሁኔ
ታ ጋር በመያያዝ ነው፡፡ማናቸውም አሳብ ቢሆን ለሕዝቡ መ
ቅረብ ይችላል፡፡ጥቅምና ጉዳቱን ዓይቶ መቀበል ወይም አለ
መቀበል የሕዝቡ ፈንታ ነው፡፡ብዝበዛን የሚቀጥልና የሚያበ
ፈፉ አሳብ ብቻ ለምን ይበሬን?

የአቶ ነጋሽ መቀባጠር በዚህ አላቆመም፡፡ኅዳር 24 በወጣ
ው አዲስ ዘመን ጋዜጣ "ትምህርትና አሳፊነት" በሚል ርእ
ስ እንቶጽ ስር እንዲህ ይላል፣"ትምህርትና አሳፊነት መ
ነጣጠል አይችሉም፡፡ ... አሁን በኢትዮጵያ የተጀመረው የ
እድገትና የልማት እርምጃ በሰላም መንገዱ —በኢቮሉሽን—
እንዲፈጠን ጠቃሚ የሆነ የአስተያየትና የአዱራጉት ዱጋፍ መ
ሰጠት ከተማረው ሕዝብ የሚጠበቅ ከፍ ያለ ሃላፊነት ነው፡፡"
እርግጥ ነው፣ትምህርትና ሃላፊነት መነጣጠል አይችሉም፡፡እና
ከሕዝቡ አብራክ የወጣን፣ዱሃው ሕዝብ ከዕለት ጉርሱ ቀጥበ
ያስተማረን ስለሆንን ምንጊዜም ቢሆን የሕዝቡ ችግር ችግራች
ን ነው፡፡የሕዝቡንም ችግር ለማሰወቅና መፍትሔውንም ለማሰወ
ቅ ሃላፊነት አለብን፡፡

አቶ ነጋሽ የሚለፍፈው ሃላፊነት የሚረባ የማይረበውን አየ
ሠሩ፣የሕዝቡን ሀብት "በሕጋዊም" ሆነ በሕገወጥ መንገዱ
መገፈፍ፣ከዚያም የተገኘው ምርት ወደመንግሥቱ የበላይ ባለ
ሥልጣናት ቢሔዱ ተራርፎ የሚወዳዱቀውን እየለቃቀሙ መኪና
መግዛትና ቤት ማሠራት፣ተቸገር አቤት ቢል ሕዝቡን መጨፍጨ
ፍና ማስጨፍጨፍ ነው፡፡ታዲያ ይህ ከሃላፊነት የራቀ የራስ
ማታለያ አይደለምን?የተጀመረው የእድገትና የልማት እርምጃ
በሰላም መንገዱ —በኢቮሉሽን— እንዲፈጠን አርቆ የሚለንስ
ምን የእድገት እርምጃ አለና ነው? የአምስት ዓመት ፕላን

አያሉ የገዥ መደብ አበሎችንና የባዕዱ ከበርቴዎችን ጥቅም
የሚያዳብሩበትን እንደሁ እኛ አንስማማበትም፡፡

የስኳር ኢንዱስትሪ ለሆላንዱ ከበርቴዎች የጥጥ ኢንዱስትሪ
ለእንግሊዝና ለሕንዱ ከበርቴዎች፣የፖታሽ ማዕድን ለሚሪካን
ከበርቴዎች፣ሆቴሎች ለልዑል መኮንን ወራሾችና ለሚሪካን ከ
በርቴዎች፣የተረፈው በሞላ ጎደል ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፎር
ጁት —የንጉሡ የግል ሀብት መሰብሰቢያ— መስጠቱ ለሕዝቡ
ምን ጠቀመው? የገሳኑ ሁሉ ወገና ጥሬት ሀብትን በጥቂቶች
እጁ ማከማቸት ከሆነ ለገበሬውና ለሠራተኛው ምን ወደቀለት?
ማደግና ማልማት ከውጭ ከበርቴዎች ጋር እየተባበሩ ሕዝቡን
መዝረፍ ከሆነ የበላም እድገት አይደለም፡፡በላሙም ሊሰፍን
አይችልም፡፡ማደግ የሚቻለው የአገሪቱ ሀብት በሙሉ ለሕዝቡ
ጥቅም ሲውል ብቻ ነው፡፡

ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል የተጻፈ አስመስለው ኅዳር
29 ቀን በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ያቀረቡት ደብዳ
ቤ፡የነዚሁ የቀጣሪዎቹ የነአቶ ነጋሽ ፈጠራ ነው፡፡ከረፍሰ
ህ ገዘ በተባለው ዘመኑ ባለፈበት ዘዴ ለመጠቀም የተደረ
ገ ፍሬ ቢስ ሙከራ ስለሆነ ምንም መተቸት አያስፈልገውም፡

## እስቲ 'ባለብሔራዊ ስሜቶች' የሚሉትን ደግሞ እንስማ

በዕውነተኛ ብሔራዊ ስሜት የተቀሰቀሰ ሪቮሉሽናዊ ኃይል እ
ያደገ መሔዱን በማየት፣የበዝባዡ ቡድን ሕዝቡን ለማበበት
ቢል "ብሔራዊ ስሜት" በሚል ፕሮግራም የሃሰት ፕሮፓጋንዳ
መንዛት ከጀመረ ጥቂት ወራት አልፈዋል፡፡በኅዳር 30 ቀን
ፕሮግራሙም ኃይለኛ የቃላት ዘመቻ ማድረጉ የሚዘነጋ አይደ
ለም፡፡

አምስት ዓመት ሙሉ ዕውነተኞቹ የኢትዮጵያ ልጆች በቁር በ
ገደል ሠላትን መደረቢ ሲያሰሙት የአሞራ ቀለብ በሆኑበት



ጊዜ ቡራቸውን ደጥረው በመሸሽ በውጭ ሲዝናኑና ሲሠፍሩ የ
ቆዩት አሁን ተመልሰው እንዴት ስለብሔራዊ ስሜት ያስተምሩ?
ብሔራዊ ስሜት የነበረውንማ ጣሊያን ጠረሰው፡፡የተረፈውን
አነሱው አጨቱት፡፡አስከር፣የዘለዓለም አገልጋያቸው አሜር ገ
ው አስተፉት፡፡ባንዳ የነበረ ሁሉ ተሰብስቦ ስለብሔራዊ ስ
ሜት ሲያወራ መስማቱ ለጆሮ ይከብዳል፡፡

እንአስመራን፣እነአቀበን ለሚሪካን እየሸጡ፣ሕዝቡን እየፈጁ
ምኑን ስለብሔራዊ ስሜት ያወራሉ? ሲሸሹ ሲይሸሹ፣በቁር በ
ገደሉ ለነፃነቱ ሲዋጋ የነበረውን ሕዝብ —በኤርትራ፣በባሌ
በጉጃም፣በሲዳሞና በተፈትም በታዎቹ— በቦንብ የሚደበድቡት
ናቸው ባለብሔራዊ ስሜቶች፡፡

ከሁሉ የሚገርመው ዕውነተኛ ብሔራዊ ስሜት ያላቸው ሰዎች
በዚሁ ፕሮግራም ቢዘለፉ መስማት ነው፡፡ኅዳር 30 ቀን ማ
ታ በዚሁ ፕሮግራም "...ማንዘራሽነትን በገሀዱ ለመግለ
ጽ ለሞከሩ...የሕዝቡንና የዩኒቨርሲቲውን ርጋታ የሚያው
ኩ፣በጣት የሚቆጠሩ ተማሪዎች...ከህሊና ወቀሳ ይልቅ ለ
ጋዊ ቀጣት ብቻ ከተሰበ ተመንገዳቸው እንደመለሳቸው የሚፈ
ልጉ ይመስላሉ" ተባለ፡፡መንግሥቱ "በጣት የሚቆጠሩትን መ
ፍራቱ የራሱን ቀራኔ፣ፍትህ የሌለው አስተዳደሩን አያሳይም
ን? ትክክለኛ፣ፍትህ የሞላበት አስተዳደር ቢኖርማ "ረብሸ
ና ብጥብጥ ያስነሳሉ ብሎ ከመሸበር ይልቅ እምነቱን በሕዝ
ቡ ጥሉ ችሎ ይል ነበር፡፡ግን ሕዝቡ መበደሉን፣መጠሉን፣መ
ብገኑን በግልጽ ያውቀዋል፡፡ለዚህ ነው "ከህሊና ቅጣ ይል
ቅ ሰጋዊ ቅጣት" የተመረጠው፡፡ለዚህ ነው ከ23 የሚበልጡ
ተማሪዎች ታህሣሥ 19 እና 20 የተረሸኑት፡፡በብዙ መቶ
የሚቆጠሩ በሰንሻ የተዘለዘሉት፡፡የአሥርና የአሥራ አምስት
ዓመት ሕጻናት የተገደሉት፡፡

በመቀጠል "ተማሪዎች እናምንበታለን፣እንመራበታለን እያሉ
የሚሰብኩት፣ሁከት የመፍጠርና ደም የማፍሰስ —ቮዳሊንስ—

ነገር ጥቅም ምንድን ነው?" ብሎ ይጠይቃል፤የብሔራዊ ስሜ
ት ልኡክን፡፡ሁከት መፍጠርንና ደም ማፍሰስን የጀመሩት እ
ነርሱ ናቸው፡፡ስለዚህም ጥያቄያቸውን ራሳቸው ለመመለስ ቢ
ሞክሩስ? የነርሱ አመፅ የሚያስከትለው፤ከሕዝቡ የሚመነጨው
ትክክለኛው አመፅ፤የገዥ መደብን አጥብ አርጉ ስለሚወስዱና
የጭቆናን ስረመሠረት ስለሚያጠፋ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትህን
ና ነፃነትን ይወልዳል፡፡መውደቂያቸው ቢሸታቸው ነው "አበዛ
ን በነጭው" እያሉ አመፅን የሚፈጽሙት፡፡ፍትህ ባለበት ሥ
ርዓት ውስጥ ገን ግንም ቨዮሌንስን አይፈልገም፡፡"የብሔራ
ዊ ስሜት" ለፈሪዎቻችን ይህን እንዳይዘነጉት፡፡

<u>እስቲ አቶ ከበደ አኒብንም እናናገረው፤እና ስተባሸረው ግለ
ት ባይሸል አይቀርም</u>፡፡

አቶ ከበደ አኒብም የዘረቱ ኢትዮጵያ በሚባል ጋዜጣው "ገ
ብ የሌለው ሤራ" በሚል ርእስ አንቀጽ ስር ቢፈተፍት "በ
ነፃ የተወለደና የኖረ ሰው የነፃነትን መታጣትና የተገዥነ
ት መንፈስ አምብዛም አይበግጠውም" ይላል፡፡ይህ አነጋገር
ነፃነት ምንድን ነው ወደሚለው ጥያቄ ይወስደናል፡፡

አቶ ከበደ አኒብ ነፃነት የሚለው ከቀኘ ገዥዎች እጅ መው
ጣታችንን ነው፡፡ጣሊያን ጊዜን ጠቅልሎ ከሔደ ወዲህ የኢት
ዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ነፃነቱን አገኘ ሊባል አይችልም፡፡የራስ
ችን ወገኖች የሆኑ፤ኢትዮጵያዊያን ነን ባዮች፤ጥቁር ፋሽስ
ቶች ተተክተው ሕዝቡ አምስት ዓመት ሙሉ በዱር በገደል እ
የተዘዋወረ የተዋጋላቸውን ሰብአዊ መብቶች ከመደምሰሳቸውም
በላይ ዘረ አገራችንን አሳልፈው ከፋሽስትም ፋሽስት ለሆኑ
ት ለሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ስለሸጧት ብሔራዊ ነፃነታችን
ን አጥተናል፡፡

በእጅ አዙር መገዛታችን ከአምስቱ ዓመት የገፍ ዘመን አገ
ዛዝ የተለየ መልክ የለውም፡፡የተለየ መልክ ቢኖር ምናልባ



ት አረንጓዴ፤ቢጫና ቀይ ሰንደቅ አላማ በየመሥሪያ ቤቱ ደ
ጃፍ ተሰቅሎ ማየታችን ነው፡፡ይህን ፊቱኑ ተገንዝበ የነበ
ረ አንዱ አርበኛ ጣሊያኖች ቢወጡና እንግሊዞች ሲገቡ ተመል
ከቶ እንዲህ አለ፡—

ነጭ አህያ ቢሔዱ ቡሳ አህያ ገባ
አርበኛው ሀበሸ ከደኑም አልወጣ፡፡

ወደጥንቱ ነገሩ መለስ ብለን እንመልከት፡፡እርግጥ የኢትዮ
ጵያ ሕዝብ የብዙ ምዕት ዓመታት ነፃነት አለው፡፡እነዚህም
የነፃነት ዘመናት ጠቃሚ ቅርሶችንና የሚያኮሩ ታሪኮችን አ
ውርሰውን ሔደዋል፡፡ነገር ግን የፊውዳሉ አገዛዝ ከናጠጠና
በተለይም የኢምፔሪያሊስቶች ተሽነክ ከገባበት ጊዜ አንስቶ
ዘጠና አምስት ከመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝብ ሙሉ ሰብአዊ
መብቱን አጥቷል፡፡ብሔራዊ ነፃነቱን ተገፏል፡፡ይኸው አሁን
ም በገረዱና በሽከር፤በገባርና በሠራተኛ፤ስም ጭብጥ የማይ
ሞሉ ጌታዎችን ሲያገለግል፤ሌት ተቀን ሲለፋና ሲኳትን ይገ
ኛል፡፡ለመሀይምነቱ ማስወገጃ ትምህርት፤ለበሽታው መፈወሻ
መዳኒት አላገኘም፡፡እንደልቡ ማሰብና መሥራት አልቻለም፤
በእጅ አዙር ለሚገዙ ባዕዳን ተሸጧል፡፡

ታዲያ ነፃነቱ የት ላይ ነው? አንዱ ጌታ ቢለወጥ ለአዲሱ
ማገልገል የጌታ ለውጥ እንጂ ነፃነት ሊባል አይችልም፡፡ነ
ፃነት ሊኖር የሚችለው ሀገር የጋራ ሲሆን፤በዝባዥና ተበዝ
ባዥ የሚለው መለያ ጠፍቶ የሰው እኩልነት ሲመሠረት፤በሽታ
ና ድንቁርና ሲጠፉ ብቻ ነው፡፡በረንዳ አዳሪውን ከአቶ
ከበደ አኒብ እኩል ነፃነት አለህ የምትሉት ውርጭ እየነፋ
ው በረንዳ ላይ ተኝቶ ለማደር በማቻሉ ይሆን? አቶ ከበ
ደ አኒብስ ነፃነት አለኝ የምትለው የበላዩችህ የሚወረውሩ
ልህን መቀበያ እጅና የሚያዙህን መስሚያ ጆሮ ስላለህ ይሆ
ን?

ለነፃነት ጥቅም ሲያትት "ሰው የማሰብና የመናገር፣የማምለክና የመማር፣የማወቅና የመመራመር ዕድል ሲነፈገውና ቢተርበት ሕይወት መራራ ይሆንበታል" ይላል፡፡እኛም የምንለው ይኸንኑ ነው፡፡እዚህ ላይ የሚያስገርመን ብቻ አቶ ከበደ አኒበ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ሰብአዊ መብቶች በሁኑ ሥርአተ ማኅበር ውስጥ እንዳሉ የጥር ተማሪዎች —ፊሽሎሽና ዊያኙ— ሲያጠፉአቸው የተነሱ በማስመሰል አሪ ማለቱ ነው፣ያሁኑ መንግሥት የሚከተለው ፖሊሲ እነዚህን ነፃነቶች መንፈግ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው፡፡

የማሰብና የመናገር ነፃነት ቢኖር ነው ትንፍሽ ያለ ሁሉ የሚረሸነው፣የሚሰቃየውና በየእስርቤቱ በሰበሰ የሚቀረው? የማምለክ ነፃነት ቢኖር ነው እስላሞችና ያልተበበሩት አንደበዐፃን የሚቀጠፉት? የሃይማኖት እኩልነት ቢኖር ነው 40 ከመቶ የማያንስ እስላም ያለበትን አገር "ኢትዮጵያ የክርስትና ደሴት ናት" እያሉ የሚለፍፉት? የኢትዮጵያ ሕዝብ እስካሁን ትምህርት እንደውሀ እየጠማው የቀረው የመማር የማወቅና የመመራመር ነፃነት ቢኖር ነው? የድሃ ልጆች ለመማር፣ለማወቅና ለመመራመር በመምከራቸው አይደለም እንዴ በለፉት ሁለት ዓመታትና ዘንድሮ ወታደር የዘመተባቸው፣በነኛ የተለተሳቸው? እንዲህም አርጉ ነፃነት የለ?

አቶ ከበደ አኒበ የዝብርቅርቅ ውሸንፍሩን በመቀጠል እንዲህ ይላል፡፡"እምነት ያሸር፣በሕል ይቅር፣ታሪክ ይጥፋ፣አንድነት ይፍረስ፣የጉሣ ስሜት ይቀስቀስ፣መታዘዝ አይኑር፣የሕግ አቷም ይደምሰስ፣መማር መመራመር፣ሠርቶ መጠቀምና በነፃነት መኖር ይወገዱ የሚያሰኝ ፍልስፍና ጉጂ ነው፡፡" ተመልከቶ የባጥ የቷጡን ቢቀበጥር፡፡የስበር ቅዝቃን ሁሉ አምጥቶ ተማሪዎች የሚከተሉት ፍልስፍና ነው ማለት የጋዜጠኛ ወግ አይደለም፡፡እኛ የምንለው ሁሉም እኩል የእምነት ነፃነት ይኑረው፣ማናቸውም ጉሣ መብቱ ተጠብቆለት፣በእኩልነት ደረጃ ሕዝቡ ራሱ በመፈቃቀዱ ዘላቂ አንድነቱን ይመሥርት፣እ



ዲስ የሕዝብ ታሪክ ምዕራፍ ይከፈት፣መማርና መመራመር፣ሠርቶ መጠቀምና በነፃነት መኖር ይመሥረት ነው፡፡ያልነበረ ከየት መጥቶ ይጠፋል? ይህ ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ስለሆነ ሕዝቡንም እንደሚያልፈው ስለምናምን ብዙ ሀተታ ሳናበዛ አናልፈቀለን፡፡

"ጥቂቶች ተማሪዎች" ከውጭ ገንዘብ እየተከፈላቸው "በዕዴ" አይዲዮሎጁን ለማስፋፋት ይጥራሉ፣የፈተና ጊዜ ሲደርስ እየጠበቁ ከፈተና ለመሸሽ ሁከት ይፈጥራሉ፣የሚል ዉሸት በመንግሥቱ ጋዜጦች ያስተጋባል፡፡ለመሆኑ "መሬት ላራሹ" የሚለው አበብ ከባዕዳን የተወረሰ ነው ወይስ የሕዝቡን ፍላጎት የሚገልጽ ነው? ለዕውነተኛ ነፃነትና ለሕዝቡ ደህንነት ጥያቄዎችን ማቅረብ፣እስከመስዋእትነት መድረስ እንዴት በገንዘብ መገዛት፣እንዴት ከፈተና መሸሽ ይባል? ጥሳሁ ገዘው የተገደለው ከፈተና ሲሸሽ ይሆን? በታህሣሥ 20 እና በሚቀጥሉትም ቀናት የተደረገው ጭፍጨፋ ፈተናን በሚሸሹ፣እየተከፈሉ የባዕዳን አይዲዮሎጂ በሚያስፋፉ ላይ ይሆን? ጆሮ የማይሰማው የለም? የኢትዮጵያ አርበኞች ሁሉ ተነስተው ይህን ቢሰሙ ምን ይሉ?

## ፍቅረ ሥላሴ ወልደሃና በተራው ይቀበጥራል

የኢትዮጵያ ድምፅ አዘጋጅ አቶ ፍቅረሥላሴ ወልደሃናም "ያንድነት ጥቅም" በሚል ርዕስ አንቀጽ ስር እንዲህ ይላል፣ "ትምህርትንና የፖለቲካ ሥራንም በአንድነት አጣምሮ መያዝ ያዳግታል፡፡ ... በሀገር ጉዳይ መጨወት፣መቀለዱ፣የነፃነትንና የአንድነትን ጥቅም አለማወቅ ነው፡፡" የፖለቲካ ሥራን ለበዝበዥ ቡድንና ለአጨፋሪዎች ብቻ ትቶ ብዝበዛው እንዲቀጥል የሚሻ የትኛው ሕዝብ ነው? በዙሪያው ያለውን በይመለከት፣በያበሳስለና ሀሳቡን በያከፍል ሊኖር የሚፈቅድ የትኛው ተማሪ ነው? ትምህርትና ፖለቲካ የማይያያዙበት ምንም ቦታ ሊኖር አይችልም፡፡የሕዝቡ ኑሮ የሚበላሽበትን መ

ነገሯ ማቅረብ እንዴት በሀገር ጉዳይ መጫወት ይሆናል? ተማሪውም ሆነ ተበዝባዡ ክፍል — በጠቅላላው ሰፊው ሕዝብ— የሚፈልገው ራሱን በራሱ ማስተዳደር እንዲችልና የጋራ ጥቅሙ በሚገባ እንዲጠቀስለት ነው፡፡

አቶ ፍቅረሥላሴ ንጉሡ ነገሥታዊ ሕገ መንግሥትን "በፈቃዱ" እንደሰጠንና ኢትዮጵያም በሥልጣኔ እርምጃ ምን ያህል ወደፊት እንደምትገፋ ካተተ በኋላ "ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ባህል ለኢትዮጵያ አይጠቅምም፤ በመጣበትና በገባበት አኳኋን በፍጥነት መውጣት አለበት፡፡ ይህንን ተከታትሎ ለማስፈጸም የሚቻለው፤ ሕዝቡን የሚወክለው ሕጋዊ መንግሥት ብቻ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ጥቅምና ዕድገት የሚቃወምን ወርሶ ለማስወገድ ካልቻልን በሳምና ፀጥታ ዋስትና አይኖረውም" በማለት ይደመድማል፡፡

ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ባህል የቱ ነው? አልገዘም፤ አልጨፍርም አልቨጥም ... ማለት ይሆን? ኢትዮጵያዊ ቢባል ሁሉም እንደአቶ ፍቅረሥላሴ ጨዋ አየባለ የሚኖር አይደለም አስከአም ቢተኛነት፤ በጥቁርም ሆነ በነጭ ጠላት አልገዛም ብሎ ማመፁ መብቴ ይጠበቅልኝ፤ ኢትዮጵያ ነፃ ትውጣ ማለት ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ባህል ነውን? ታዲያ በዱር በገደሉ አሁንም በመትረየስና በቦንብ የሚፈጁት፤ ሥልጣንን በጠበጡ ተበዮች የተገደሉትና ለነፃነት ቢሉ በየእስር ቤቱ የሚማቀቁት ሁሉ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ባህል በመከተላቸው ነዋ? ዝም ብሎ መገዛት ከመቸ ወዲህ ነው የኢትዮጵያ ባህል የሆነው?

<u>ብርሃኑ ጥበቡ፤ የሔራልዱ አዘጋጅና የአሜሪካኖች የጡት ልጅ ሌሎች ጋዜጠኞች ዳሩን ቢነኩት የኖቁትን፤ የመንግሥትን ምሽት ቅልጥ አድርጉ ያስተምጥልናል</u>

"የኢትዮጵያን" ሔራልዱ ጊዜያዊ አዘጋጅ አቶ ብርሃኑ ጥበቡ ታህሣሥ 4 ቀን በወጣው ጋዜጣው ጌቶችን <u>በይበልጥ</u> ለማስደ



ስት <u>ይበልጥ</u> ጥሯል፡፡ ከሁሉ የሚያስደንቀው "ለጥቂቶች ጥቅም ብሎ የብዙዎች ሀሳብ አይገለጽም፡፡ መጽሔቱ —ታገል— የጥቂቶቹን አስተያየትና ፍላጎት ብቻ ነው የሚገልጸው" ማለቱ ነው፡፡ ታገልም ሆነ ሌሎቹ የተማሪዎች ማኅበራት መጽሔቶች የሚያቀርቡት ሀሳብ የመላውን ሕዝብ ደህንነት የሚሸ ቢሆን የመላው ተማሪ ድጋፍ አይለየውም፡፡ የሀሳብ አንድነት ባይኖርማ ይህ ሁሉ ተማሪ በአንድነት ሆኖ መች ይጠፋፋ ነበር?

ነፃነት የተጠየቀው በጥቂት ተማሪዎች ሳይሆን በመላው ተማሪው፡፡ በተማሪዎችም ብቻ አልተገታ፡፡ ሕዝቡ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፤ ከሰሜን እስከደቡብ የሚያስተጋባው ይኸንኑ ጥያቄ ነው፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ የተማሪዎችን ጥያቄ ከሰፊው —ከተራው— ሕዝብ ጥያቄ ለመነጠል መሞከር ከንቱ ድካም መሆኑን እነሱም ያውቁታል፡፡ "ታገልን" የከለከሉት የጥቂት ተማሪዎችን ብቻ ሳይሆን የመላውን ሕዝብ ጭምር እንደሚያስተጋባ ተገንዝበውት ነው፡፡

ብርሃኑ በሌሎች ጋዜጦች ተደጋግሞ የተጻፈውን ዝብዝንኪ ካስተጋባ በኋላ "መንግሥቱ "በታገል መከልከል ብቻ መቆም የለበትም፡፡ የተጀመረውን ሥራ እስከመጨረሻ ገፉ ማድረስ አለበት" ቢል ይደመድማል፡፡ የመጨረሻ ገባቸውንም ታህሣሥ 29 እና 30 አበቁን፡፡ እዚህ ላይ ልናስታውሳቸው የምንሻው "የመጨረሻ ገብ" በማለት የወሰዱት እርምጃ የነሱኑ መቃብር ቆፈራ ከሚያፋጥኑት ድርጊቶች አንዱ መሆኑን እንዲገነዘቡት ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ጋዜጦች በሙሉ እርምጃ ይወስዱ፤ መንግሥት አንዱ ነገር ማድረግ አለበት፤ ይህን ሕገወጥነት ለመመለስ መንግሥቱ በኃይል እንዲጠቀም ይገደዳል እያሉ ፊቱ የተጠነሰሰውን ሤራ በምክር መልክ ያቀርባሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የጋዜጣ ዘመቻ ሲደረግ የመጀመሪያው ጊዜ ነው፡፡ ይህ

ሀብብ ከየት መነጨ አሳማውስ ምንድን ነው ብለን ብንጠይቅ መልሱ ሩቅ አይሆንብንም::

ወደፊት ተራማጁ ይሉ ከሁኑ መቀጨት እንዳለበት ትእዛዝ የተላለፈው ከመንግሥቱ የበላይ ጠባቂ ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ቢሆን ይህንኑ ትእዛዝ አገቡ ለማድረስ ታጥቀው የተነሱት ታዛዦቹም ደግሞ ሥልጡንነታቸውንና አረመኔነታቸውን ማስመስከሪያ ዕድል አገኙ::ያገር ግዛት ሚኒስትሩ ዘውዴ ገብረ ሕይወት፣የፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ ይልማ ሽበሺ፣የአዲስ አበባ ከንቲባ ኃይለጊዮርጊስ ወርቅነህና እንዲሁም አንዳንዱ ሌሎች ባለሥልጣኖች ከገዥው መደብ መሪዎች የተቀበሉትን ትእዛዝ ጋዜጠኞችን ሰብስበው "በተማሪዎች ላይ ኃይለኛ እርምጃ ልንወስድ ነውና በጋዜጦቻችሁ ሕዝቡን አሰናቁልን" ቢሉ አስተላለፉ::

ጋዜጦች በሙሉ ደጋግመው የሰጡት መልእክት አንድ ዓይነት መሆኑ አበቡ ከአንድ ቦታ መፍለቁን ያሳያል::ከዚህም ስብሰባ የተሰጣቸውን ትእዛዝ እንደተፈለገው በማከናወናቸው የመንግሥት ጋዜጠኞች ትንሽ ጉርሻ ባይሰጣቸው አይቀርም::ወይም እስከ አሁን ተሰጥቷቸው ይሆናል::

አባብ አመንጭዎቹም ሆኑ አስተጋቢዎቹ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ኃይለኛ የጋዜጣ ዘመቻ ለማድረግ ሞክረዋል::እንዳሰቡት መልእክታቸው ተቀባይ አላገኘም::ለሙከራቸውም ወደፊት ሕዝቡ በሚገባ እንደሚከፍላቸው አይጠረጠርም::

የወንዶቻችንና የእህቶቻችን ደም ይጮሀል

አስገዳዮችንና ገዳዮችን በሙሉ እንበቀላለን

ትግላችን ይቀጥላል

---

1 ታጠቅ ልዩ ቅጥር፣ጥቅምት 1962፣አገሪቷና ኢኮኖሚዋ ክፍል 1 ተመልከት

2 ታጠቅ ልዩ ቅጥር፣ጥቅምት 1962፣አገሪቷና ኢኮኖሚዋ ክፍል ሁለት ተመልከት



## ከአገር ቤት የደረሱን ዜናዎች

### ሁ. የወዝ አደሩ መታጎሪያ እስር ቤት

አገር ቤት ባሉ አነበቢዎቻችን በኅብረት ተጠንቶ የደረሰን

የኅብረተሰቦች ታሪክ በሙሉ እንዳሳየውና አሁንም በየቦታው በየዕለቱ እንደሚታየው መውደቂያው የደረሰ መንግሥት የሰፊ አደሩን የረቮሉሽን ማዕበል ለመግታት ቢል ፋሽስታዊ የሆኑ እርምጃዎችን በግልጽ ይወስዳል::ይህም ጊዜ ያለፈበት ሥርዓተ መንግሥት የሚለይ ጠባይ ቢሆን ውጤቱም የለውጥን አቅጣጫ ማቅረብ እንጂ ረቮሉሽንን ማዳከም አይደለም::ዛሬ በኢትዮጵያ ሰፊ አደር ሕዝብ ላይ የሚደርሱት ልዩ ልዩ በደሎች የሚያመለክቱት የለውጥ ቀዜማ መጠጋቱን ነው::

ወደመውደቂያ ያዘመመውን የኢትዮጵያን መንግሥት ፋሽስታዊ ይዘት በግልህ የሚያበዩ ብዙ ምልክቶች አሉ::በዚች በጭሯ ጽሑፍ ችን ውስጥ ለማቅረብ የምንፈልገው ግን በጃንሆይ አኛ ታፈነ የሚታጎረው ሕዝብ በወህኒ ቤቱ የሚደርስበትን ስቃይና መከራ ነው::

በዝባዡና ተበዝባዡ መደቦች ባሉበት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኝ ወህኒ ቤት ሊኖረው የሚችለውን ባሕርይ ማንም ሊገምተው ይችላል::መብት ያለው የትኛው ወገን፣ይህንኑስ መብት አስከባሪ የትኛው ኃይል እንደሆነ ማወቁም አያስቸግርም ብለን እንገምታለን::ሕጉን አውጭው፣አስፈጻሚውና ተርጓሚው የበዝባዡ መደባዊ ክፍል እንደመሆኑ መጠን ሕጉ ወደየትና ለማን እንደሚያደላ መረዳት አያውክም::

በአሠሪና በሠራተኛ፣በበዝባዡና በተበዝባዥ መደቦች መካከል ያለው ቅራኔ በከረረ ቁጥር እርቅ የለሽ ትግላቸው ይጧጧቃል::በዚህን ጊዜ እንበዝበዝም፣እንጨቆንም ብሎ የተነሳው ሕዝብ፣የበዝባዦችን ጥቅም ለመጠበቅ በተሠራ ሕግ አማካይነት፣ወንጀለኛ ተብሎ በየእሥር ቤቱ ይወረወራል::

ስለዚህም ትግሉ እየተፋፋመ በሔደ ቁጥር በዝበዛው መደብ አልበዘበዝም ብሎ የተነሳውን የወዝ አደር መደብ የሚያጉርበት እስር ቤት በብዛትና በስፋት ማዘጋጀት ግዴ ይሆንበታል

ዛሬ በኢትዮጵያችን የምናየው ይኸንኑ ሁኔታ ነው::ሕዝቡ በያለበት ከመነሳቱ የተነሳ አድሃሪው መንግሥት በያለበት የማጎሪያ ቤቶን አዘጋጅቶ ላብ አደሩን ያለአንዳች ወንጀልና ፍርዱ ከያለበት እያፈሰ ያጉሩዋል::የእስር ቤቶን ሁኔታ አስቃቂነት መቼም አታንሱ::የደቡብ አፍሪካ ወንጀሎቻቸን ከሚሰቃዩበት ከፕሪቶሪያን የቀኝ ገዥዎች እስር ቤት ጋር ሲነፃፀር ይችላል ብገል ከዕውነቱ የመንርቅ አይመስለኝም::የታወቁ ሲቶች በቀርቡ አጥንተው እንደደረሱበት ለጊዜው በምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ በይዘታው አስቃቂነትና በእሥረኞች ቁጥር ብዛት <u>የኢትዮጵያ ወህኒ ቤት አንደኛ መሆኑ</u> ተረጋግጧል::

ከዚህ በታቾች በአገር ቤት ያሉ አነበቢዎቻችን በኀብረት አጥንተው የደረሱበትን የእስረኞች ቁጥር አነስተኛ ግምት እና ቀርባለን::

| | | |
|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | |
| | ወህኒ ቤት | 5000 |
| | ጣቢያ | 2500 |
| 2 | ሸዋ ጠቅላይ ግዛት | 3500 |
| 3 | ጎጃም ጠቅላይ ግዛት | 5000 |
| 4 | በጌምድር ጠቅላይ ግዛት | 2000 |
| 5 | ኤርትራ ጠቅላይ ግዛት | 3500 |
| 6 | ትግሬ ጠቅላይ ግዛት | 2000 |
| 7 | ባሌ ጠቅላይ ግዛት | 3000 |
| 8 | ሐረር ጠቅላይ ግዛት | 2700 |
| 9 | አሩሲ ጠቅላይ ግዛት | 2000 |
| 10 | ወለጋ ጠቅላይ ግዛት | 2000 |
| 11 | ከፋ ጠቅላይ ግዛት | 1500 |
| 12 | ኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት | 4000 |
| 13 | ገሙ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት | 2500 |
| 14 | ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት | 1500 |



የኢዴገት ማሰፈሪያና ያገር ማሸሽያ አንቶስትሪ ይመስል በአገራችን በያለበት በተቋቋመው እሥር ቤት ውስጥ ያለውን የሚያስመርር ኑሮ ከዋሳ ጉደል በዓይናችን አይተነዋል::ምስክርነታችንንም ለመስጠት አናፈገፍግም::ለምሳሌ ያህል በቅርቢያችን ያለውን የአዲስ አበባውን ወህኒ ቤት ሁኔታ እንመልከት::

<u>ሀ.ብዛት</u>

በአዲስ አበባው ወህኒ ቤት ውስጥ ከ5000 በላይ እሥረኞች መኖራቸውን ያውቃሉን? ከዚህ ቁጥር ውስጥ ከግማሹ በላይ ያለፍርዱ የታሠረና በቀጠሮ ብቻ ከ10 — 13 ዓመታት የተንገላታ ነው::በየቀኑ የሚጨመረው የእሥረኞች ቁጥር ከ10 — 20 የሚደርስ መሆኑ ተረጋግጧል::

<u>ለ. ምግብ</u>

ለሃያ አራት ሰዓት <u>የሚለገስ</u>

1 ቀቀርሸ የሚመስልና የሚያስመስል አንዴ ጭልፋ የገብስ ቆና — ቁርስ

2 አንዱ የተቀያየጠ ራስ የሚያዝር ርሚጦ ቲጨና አንዱ ጭልፋ የደቀ ብጥብጥ አልጫ — ምስ

3 የምበውን የሚመስል አሬት፡፡የሚሰጠው በምበ በዓት ላይ ነው፡፡

4 ልዩ ምግብ ተብሎ ለክርስቲያኖች የዐሑዴ ምስ፣ለእስላሞች የአርብ ምስ ይሰጣል፡፡የማዕዱኑ ይዘት፣ አንጀት ሳሊስ የምታህል ልፋጭ ስጋና አንዱ ጭልፋ መረቅ ተመስ ሸርቢ — ውሃ፣እንዲሁም አንዱ በጣም ከበካ የቀቀር ጨፍና ዘንጋዳ የተጋገረ እንጀራ ከአንዱ ጭልፋ የደቀ አልጫ ጋር፡፡

## ሐ. ልብስ

እሥረኛው ከቤቱ ከሚያመጣው ልብስ በስተቀር ምንም ዓይነት ልብስ በእሥር ቤቱ አይሰጥም፡፡በተለይ በዚያ በሲሚንቶ ቀዝቃዛ ላይ ሌሊት የሚነጠፍ ሆነ የሚለበስ ወይም የሚደረብ ልብስ የለም፡፡ስለዚህ ከቤቱ ለማስመጣት የማይችለው አብዛኛው እሥረኛ ከቁሳ ጉደል አርቃን ሥጋውን ይገኛል፡፡

## መ. ቤቶች

በከተማው ማህከል የሚገኘው ከምሥራቅ አፍሪካ ትልቁ እሥር ቤት የተሠራው በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ሳይ ሲሆን መሐንዲሶቹም በዚያን ሰሞን ቀኝ ግዛት ለማግኘት ይቅበዘበዙ የነበሩት መሐንዲሶች ናቸው፡፡የእሥር ቤቱም ይዞታ ይሆነኝ ተብሎ ለጭቆናና ለስቃይ የተሠራ ነው፡፡ከዚያ ወዲህ በግቢው ውስጥ የተሠመረ ቤት ቢኖር መያተኛ የሚውሉበት አንዱ አዳራሽ ብቻ ነው፡፡በዚያን ጊዜ የተሠራው የቀንቶ እሥር ቤት በዚያን ዘመን የነበሩትን እሥረኞች ብቻ እንዲይዝ ተደርጎ ነው፡፡በዚያን ጊዜ ስንልም፣እንደዚሁ እ



ንደዘረው ወንጀል በተራቀቀ ዘዴ አይፈጸምም፣በዝባዡ መደብ ተበዝባዡን ሆነ ብሎ አይከረኩምም፣ዝሙትና መሸታ፣ተንኮልና ከፋት እንደዘረው አልተስፋፋም ነበርና የእሥረኛው ቀጥር የተወሰነ ነበር፡፡እንደ መንጋ ለሚታጎረው ለዘመኑ እሥረኛ ለዱርዬዎች እሥረኞች የተዘጋጀው ቤት ይበቃል ብሎ ማመን ከነሷና ገምት በላይ ነው፡፡የሠርዱን ታሪክ ነው፡፡የቤቶችን ሁኔታ ለማበየት ያህል፣

ወህኒ ቤቱ በሦስት ዋና ክፍሎች የተመደበ ነው፣

### 1 ዓለም በቃኝ

ይህ ክፍል ነፍስ ገዳይና ዕዴሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው፣ እንዲሁም ያመለጡ ተብለው የሚፈሩ የፖለቲካ እሥረኞች ታፍነው የሚቀመጡበት ክፍል ነው፡፡ከበ ሕንጻ ቢሆን ዙሪያውን መርፌ የምታሾልክ እንኳን ቀዳዳ የለውም፡፡ውስጡ ባለአንዱ ፎቅ ነው፡፡52 ክፍሎች አሉት፡፡በነዚህ ክፍል ውስጥ በያንዳንዱ ከ7 — 10 ሰዎች ይቀመጡታል፡፡በአነስተኛ ቀጥር በየጊዜው 500 ሰው አይጠፋበትም፡፡ከሰማይ በስተቀር ምንም የሚታይ ሌላ ነገር የለም፡፡በዚህ ውስጥ ምናልባት ከ15 — 20 ዓመታት በፊት ሞት ተፈርዶባቸው እስካሁን ሞታቸውን ገና የሚጠባበቁ ይገኙበታል፡፡ከአሁዱ በስተቀር ለፋብ በዓት ያህል እንኳን የሚያጠግብ አየር አገኝተው አያውቁም፡፡ዕውነተኛው ዓለም በቃኝ ነው፡፡በውስጡ ከ20 የማያንሱ አብዶችም ይኖራሉ፡፡ሽንት ቤቱ አንዱ ነው፡፡ግቢው ከ200 ካሬ ሜትር አይበልጥም፡፡ሌሊት ይቀዛቅዛል፡፡ቀን ይወብቃል፡፡

### 2 ቀጠሮ ቤት

ይህ ክፍል አብዛኛው እሥረኛ የሚገኝበት ክፍል ነው፡፡ሦስት ትላልቅ አዳራሾች ሲገኙበት እያንዳንዳቸው ከሁለት ቦታ ላይ ተከፍለው በውስጣቸው 500 ሰዎች ይገኛሉ

በስድስቱ ክፍሎች ውስጥ 3000 እሥረኞች ይገኛሉ ማለት ነው፡፡እንዳየነው ከሆነ ከሰው መጨናነቅ የተነሳ እግርን ዘርግቶ መተኛት አይቻልም፡፡የዓየሩ መታፈን አይነሳ፡፡ውሀ ለማግኘት፣ሽንት ለመክፈል፣ፀጥታ ለመሽትና ለመቧበሰው ጥያቄ በዚያ ውስጥ መልስ አይገኝለትም፡፡ በሽተኛም ቢኖር ሞት ከመጠበቅ በስተቀር ሌላ ምርጫ የለውም፡፡በተወሰኑ ሰዓቶች ውጭ ወጥቶ መናፈስ ቢፈቀድም የውጭ ጥበት የዚያነው ያህል አያዝናናም፡፡እሥረኛው ከምሬት ብዛት የተነሳ የሕሊና ጤንነት ከቶ አይነበበትም፡፡መሠቃየት፣መሠቃየት አሁንም መሠቃየት ነው፡፡በዚህ ክፍል ውስጥ በቁጥር ብቻ በመመሳሰስ ከ10 — 15 ዓመት ያደረገ ይገኛል፡፡አብዛኛው ነው ማለትም ይቻላል

3 ፍርደኛ ቤት

ትንሽ ፋታ የሚገኝበት ቦታ ይህ ክፍል ነው፡፡በቤት ረገዱ ማለታችን ነው፡፡የአንጨት ቆጦች አሉት፡፡መጠነኛ አዳራሽ ነው፡፡ቁጥራቸው ከሰባት አያንስም፡፡ለበዝበዙ መደብ እንደያገለግል ብሎ በየሙያው እየተሰማራ የጉዳጁ ሥራ ሲሠራ ይውላል፡፡ሲሔዱ በጠበመንሻ ታጅቦ ነው፣ሲመለስ የሚመገበው ያው የጠቀሰነው ምግብ ነው፡፡በተረፈ ሌላው ሁሉ ከሌሎቹ ጋር ይመሳሰላል፡፡ቁጥሩ ከሺህ አምስት መቶ በላይ የሆነ እስረኛ ይገኛል፡፡

ሠ. አድልዎ

በበዝበዙ የገዥ መደብ የሚፈጸሙት ነገሮች ሁሉ በወህኒ ቤቱ ውስጥ ወለል ብለው ይታያሉ፡፡ከጥቅም ገጭት የተነሳ እንዳንዱ የበዝበዙ መደብ ወገኖች ቢታሠሩ በገንዘብ ኃይል ብቻ እነዚህ ሰዎች የእሥር ቤቱን መልክ ይቀይሩታል፡፡አልጋ ያስገባሉ፡፡ውጭ ወጥተው ከቤት ይገናኛሉ፡፡ሌላም አስፈላጊ መስሎ የታያቸውን ዕቃ ሁሉ ሊያስገቡ ይችላሉ፡፡የሕክምና



መስጫ ብሎ በተለይ ለበሽተኞች የተዘጋጀ ክፍል አለ፡፡እነዚህ የበለው ወገን እሥረኞች አስከወጡ ድረስ ያን ክፍል እንደአልፍኛቸው አርገው ይጠቀሙበታል፡፡

ባንዳንዱ ምክንያቶች የተነሳ እዚህ ላይ ልንጠቅስ የማንፈልጋቸው ልዩ ልዩ የአድልዎ ዓይነቶች እንደሚፈጸሙ የሚያውቀው ሁሉ ያውቀዋል፡፡እንዲህ ያለው የወህኒ ቤት ድርጊት ያለ ምክንያት የታሠረውን የወዝ አደሩን ወገን የሚያበሳጭና የሚያበግኑ የአእምሮ ደዌ ነው፡፡መሆኑንም ደርሰንበታል፡፡

ረ. ቅጣት

እሥረኛው በሆነ ባልሆነው የሚቀበላቸው ብዙ ዓይነት አሰቃቂ ቅጣቶች አሉ፡፡ምክንያት እየፈጠሩ የሚፈጽሙት አብዛኛ ድርጊት በው መሆኑን ያስጠላል፡፡ከዱብደበውና ከሌላው የቅጣት ዓይነት በላይ እሥረኞች የሚሰቃዩባቸውን የማሠሪያ ዓይነቶች ልንገልጽ እንወዳለን፡፡ከብረት የተሰሩ ስድስት ዓይነት ሰንሰለቶች ቢኖሩ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ ቀጥለን የምንዘረዝራቸው ናቸው፡፡

1 ጃብ

የመሠረሸ አጥሬ ቢበል፣እግሩ ተክርችሞ የሚታሠርበት ሥጋን አልፎ አጥንትን የሚፍቅ ሰንሰለት ነው፡፡እግሩ ላይ የሚታሠረውም ቀለበት በመዶሻና በመሬሻ እግሩ ላይ እንዳለ ተቀጥቅጦ ነው፡፡ሰው ካልተሸከመው በስተቀር በጃብ የታሠረ ሰው ሊንቀሳቀስ አይችልም፡

2 ማሚቴ

ከጃብ አነስ ያለ የእግር ብረት ነው፡፡ቀለል ከማለቱ በስተቀር ዓይነቱ የጃብ ተመሳሳይ ነው፡፡

3 ካቴና

የላይኞቹ የእግር ቢሆኑ የኸኛው የእጅ ነው፡፡ዓይነቱም

በ15ኛው መቶ ዓመት ጨካኞች ቅኝ ገዥዎች የሚጠቀሙበት
ን ይመስላል፡፡ቢቆለፍና ቢከፈት በብዙ ትግልና መከራ
ነው፡፡

4 አገሬ ሙቅና በነበለት

ይህ ደግሞ አሥረኛውን እንደ ዘጠኝ አህዝ ቅርጽ የሚያ
ሰኙ መሣሪያ ነው፡፡በእርሱ ታስሮ እንቅልፍ መተኛት
አይቻልም፡፡በሽቦ ከታሠሩ በኋላ ከቴናውና ጃቡን በበ
ነበለት አኖሬኝቶ ማሠር ነው፡፡ይህን የቶመሰ በው የም
መኪዶ ያጠፈጥፈል፡፡ጤንነትም ቢሆን የስትና የለውም፡፡

ሰ፡ አዲስ አሥረኛ ሲገባ የሚያየው ፍዳ

የገዱ የሚያልፍበቸዉ በሮች አሉ፡፡ከጨቢያ ወይም ከወሬዳና
አውራጃ ግዛት እሥር ቤቶች እንደመጣ በሽታ ይዞ እንዳይገ
ባ በደንዘዘ መርፌ የሾየ መድኃኒት ይወጋል፡፡ራሱ የተወጋ
በት ቦታ አበጦ ቢያማቅቅ ሚጥሮር ልቅ ደዌ ነው፡፡

ከዚያ ቀጥሎ 'ሹህ ገዓይ' ከሚባል ሥፍራ ይደርሰል፡፡የተ
ባይ ማጥፊያ መድኃኒት የሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡በዚህ ሥፍ
ራ ውስጥ ዘመኑ የማይታወቅ የከረከሰ መሣሪያ አለ፡፡አሥረ
ኛው ያለውን ልብስ ሁሉ አውልቆ በጥቶ ለአንዱ በዓት ያህ
ል እርቃኑ ሥጋውን ይቆማል፡፡ልብሶቹ በረጃው መሣሪያ ውስ
ጥ ገብተው በበበበበ የተባይ ማጥፊያ መርዝ ውስጥ ይታጀ
ሉና ይመለሱለታል፡፡ለወጉ ነው እንጂ ተባይስ ይዘው የሚመ
ጡት ከመሣሪያው ውስጥ ነው፡፡የትባይ ማጥፊያ መድኃኒት ከ
ገማቱ የተነሳ አፍንጫ በጥብ ይጥሳል፡፡

ከዚያም ጸጉሩን በደንዘዘ ምላጭና ፀጉር በሚነጭ የተረባ
ከሲጦር ለመላጨት ወደሌላ ቦታ ይመራል፡፡የጉፈረው ፀጉ
ያልውሃ በደረቁ ፀጉሩን ይላጨል፡፡መላጨት ባይሆን ይገጠብ
ል፡፡ከዚያ አከሉ ዘሩ በይቶር ተፈትሾ ወደመታጉሪያው ስፍ



ራ ይሳካል፡፡በእሥር ቤቱ ውስጥ በሚኖርበት ወቅት በየሁለ
ት ሳምንቱ ራሱን ሲገጠብ ይኖራል፡፡

ዘመዱ እዝማዱ ያለው እሥረኛ ሽይም ቡናም በጉቦ እያስፈላ
ሊጠጣ፣ምግብም ሊያገኝ ቢችል ሌላው ግን በተወሰነው መኖ
ቢማቀቅ ይኖራል፡፡ስቱኒኛ —ሽይ አፍሊ— ለማግኘት ከሚገበ
ው ስንቅ ማከፈል ይኖራል፡፡ልብስ ማጠብና ንጽሕናን መጠበ
ቅ ከውሃው ውዱነት ጋር የተዛመደ በሰሆነ ፍጹም ለማድረግ
የማይቻል ነገር ነው፡፡ማድረግም የሚችሉ ቢኖሩ ትልቅ ዕዱ
ል ያሳቸው ናቸው፡፡

ብዙ ዘመን የመታሠር ዕድል ያሳቸው በፆች የአልቀና ማዕር
ገ በሰሚሰጧቸው እሥረኛውን በዚያው ሁኔታው ላይ ለመመጥመ
ጥ አይመለሱም፡፡ለየምክንያቱ ሁሉ ጉቦ ይፈልጋሉ፡፡እንደሚ
ባሰውማ አዚያ ውስጥ ሆነው በሚያገኙት የጉቦ ገንዘብ ውጭ
ታሳሳቅ ሕንፃ አሠር ተቀል ይበላል፡፡

ይህ አጭር መግለጫ ስለአዲስ አበባው ወህኒ ቤት ቢሆን በ
ሌላ ቦታ በሚገኙት እሥር ቤት ውስጥ ግን ያለው ሁኔታ ከ
አዲስ አበባው አምበ ጊዜ የከፋ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በተለይም
ለአሥረኛው ምግብ የማይበጠው በመሆኑ ስንቅ የሚያቀርብ ወ
ገን የሌለው ሁሉ በረሃብ እንደሚልቅ ጥናታችን ደርሶበታል

ይህ ዓይነቱ የእሥር ቤት ስያይ የፊውዳሉ መንግሥት አንዱም
ቀጥተኛ ውጤት ነው፡፡ይህም ሥርዓተ መንግሥት እስካለ ድረ
ስ ይቀጥላል፡፡መፍትሔው የሚገኘው ፊውዳሉ መንግሥት በኃይ
ል ተደምስሶ ወዴቸ በቦታው የሰብ አደሩን መብትና ጥቅም
የሚጠብቅ መንግሥት ሲተካ ብቻ ነው፡፡

እንዱነታችንን በማጠንከር ለሕዝባዊ መንግሥት እንታገል

## ለ. የነጋዴዎች አሉሳ መታሠር

እንደኢትዮጵያ በሠለጣ ዘመን አስተዳደር ውስጥ በሚኖሩ አገሮች ነፃ ጋዜጣ፣ወይም ራዲዮ፣ወይንም ቴሌቪዥን የሉም፡፡ የመንግሥቱ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች — ጋዜጣው፣ራዲዮው ወይም ቴሌቪዥኑ — ስለዓለምም ሆነ ስለአገራችን ሁኔታ ስሕዝቡ የሚያቀርቡቸው ዜናዎች በወንፊት ተነፍተው የገዥውን መደብ ጥቅም የማይነኩ መሆናቸው የተረጋገጠላቸው ዜናዎች ብቻ ናቸው፡፡ "ሲገበር" ይባላል፡፡

ስለዚህም አንዱ ወሬ በተገኘ ቍጥር ያው ከፍ ወደአፍ እየተሰራፈ ዕውነቱና ውሸቱ ተደበላልቆበሕዝቡ ዘንድ ይናፈሳል ይህ ታዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተፈጥሮ "ወሬ ወዳጅ" ወይም "ወሬ ፈጣሪ" ስለሆነ አይደለም፡፡ የመናገርና የመጻፍ፣ የማሰብም አገዛዝ ነጻነት በሰፈነበት አገር ይህ ዓይነቱ የወሬ መነዛትና መዘበራረቅ የተለመደ ነው፡፡ በሌሎች ሕዝቦች ታሪክም ውስጥ ተደጋግሞ ደርሷል፡፡ ...

የሆነ ሆኖ በቅርቡ ከአዲስ አበባ በደረሰን ዜና መሠረት ደጃች አሉሳ —የብሔራዊ ፀር ኢታ ማዦር?—፣ጀኔራል በመኮል፣ ኮሎኔል ስሜን በዶር፣ የመቶ አለቃ አስታጥቀነበርበር መኮንን —ሬ ዓት ሚኒስትር— እንደዚሁም በርካት ያሉ የፀር ኃይል ባለ ደረቦችና ቢሮሎች ተይዘው ታስረዋል፡፡

እንደሚወራው ከሆነ እነደጃች አሉሳ የተከሰሱት "የመንግሥት ገንዘብ ሰሳመፉ" ነው፡፡ በዚህ ክስ ላይ እስከታች በሌብነና በጭበርበራ በተሞላ ቢሮክራሲ ውስጥ እንኳ ሌላውን በር ቶሀ ሉ ብሎ መክሰቡ አስቂኝ ነገር ነው፡፡ በጥኑ የሚነዛው ወሬ ደግሞ "በመንግሥቱ ላይ ሲያምፁ ቢዘጋጁ ተይዘው" ነው ይባላል፡፡ ዕውነቱ ይኸ በይሆን አይቀርም፡፡

ወጣም ወረደም የነጌሎ ተኛ አጁና "ታማኝ አገልጋይ" የነ



በረው ሁሉ በጊታዉና "በታማኝነቱ" በመኑት ላይ እጅጉን ማኅሰቱ በገዥው መደብ ውስጥ ያለው የሥልጣን ሽሚያ መፋፋሙን እንደሚያመለክት አንጠራጠርም፡፡ እንዱ ተረት እንደሁ ይባል፡፡ የኖሩበትና ያኖሬቸው መርከብ እንደሚሰምጥ ሲሰማቸው ከሰዎች ቀደመው ከመርከቡ አንዱ በንዱ የሚሸሹ አይጦች ናቸው፡፡

---

## የታህሣሥ 19ና 20 አልፂት ያስከተለው ሬቮሉሽናዊ ደያ

በነዚህ በማይረሱ የአልፂት ቀናት እንደጉርፍ የወረደው የ
ወንድሞቻችን ደም በመላው የኢትዮጵያ ተማሪና ሰፊ ሕዝብ
ላይ ከፍ ያለ የሀዘን ነዲት አስዴርቦታል፡፡እዚህ ላይ አ
ንድ የማይካድ ዕውነት አለ፡፡ይህ ነዲትና ሀዘን ወንድሞቻ
ችን የተቀበሉትን ሬቮሉሽናዊ መስዋዕትነት ለመቀበል የሚዘ
ጋጁት ሬቮሉሽናዊያንን እንደሚያበዛ ስይታለም የተፈታ ነው
ይህን በለፈው ትግላችን ውስጥ ያለእንዳች መጠራጠር ተናገ
ረንዋል፡፡አሁንም እንናገረዋለን፡፡

ለዚህም፣አልፂቶ በውጭም ሆነ በውስጥ ያቀጣጠሳቸውንና በመ
ሩፉም ላይ ያሉትን የተቃውሞና የማጋለጫ ትግሎች ከመመልከ
ት ሌላ በቂ ምስክር የለም፡፡

እዚህ ላይ የአዲስ አበባ ወንድሞቻችን በሞኑን በወጡት ጽ
ሑፍ ላይ የትግሉን ታሪካዊ ዕድገት በማጠቃለል የሰጡትን
መግለጫ መጥቀስ ሁኔታውን በበለጠ በያብራራው አይቀርም፡፡

"መጀመሪያ የወረደብን የፖሊስ ዱላ ነበር፡፡ወዲያውኑ ስለ
ተለመድነው ለመቋቋም ጊዜ አልፈጀብንም፡፡ቀጥለው የተጠቀሙ
በትን የቦምብ ጢስ ወዲያውኑ ተለመድነው፡፡አሁን በጥይት
መጠቀም ጀምረዋል፡፡ግን ይኸንንም እንለመደዋለ፡፡"

ጥያናው በበሰ ቅጥር የታገቀ ሬቮሉሽናዊ መንፈስና ቸሬጥን
ት በጥፍ እንደሚያዱግ ቅልጥ አድርጉ የሚያሳይ ዕውነተኛ
አነጋገር ነው፡፡ገና ታንከኞቻቸውና አይሮፕላኖቻቸው ጭምር
ይለመዷሉ፡፡በዚያን ጊዜ በሌላ በምን ይጠቀሙ ይሆን?በዚያ
ን ጊዜ ምን ይወጣቸው ይሆን?

ቀጥለን አልፂቶን በመቃወምና ሬቮሉሽናዊ ትግሉን በመደገፍ
ከተወሰዱት እርምጃዎች አንዳንዶችን እናቀርባለን፡፡



## ሀ. ባገር ቤት የተወሰዱ የተቃውሞ እርምጃዎች

### ገ የቀነበርስቲው፣የሁለተኛና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለሕዝብ የበተኑት መግለጫና ለፊውዳሉ መንግሥት የደረደሯቸው ጥያቄዎች

ትክክለኛ ገልባጭ

### የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዱምስ

ፋሽስቱማ ይባል ገረፈው ገረፈው
ገብረእበሩም ይባል ተሸን ገደለው
ወዮላሽ፣ደም መላሽ ሲመጣ ኋላ ምን ይውጠው

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈጸመው በደልና ገፍ ከዕለት ወ
ደዕለት እየተገለጸ ሔዶ አሁኑን እርቃኑን ሆኖ በጥያቄ ም
ልከት ተፈጦ፣መላ ቀጡን አጥቶ ቀሞአል፡፡ይህ ከደቡብ አፍ
ሪካና ከሮዴዚያ የበሰው ተቀበዝባዥና የሚጨበጠውን ያጣው
ፋሽስታዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ተማሪዎች፣ሠራተኞች እንዲሁ
ም በዝጠቀነው በገበሬ ቸስቷሽነት ጤና ካጣ ብዙ ጊዜ ቢሆ
ነም በቅርብ ጊዜ የቸስቷሽነቱን እርምጃ አሬሱ በመውሰዱ፣
የገፍ ድርጊቱን በመፈጸም የሚቀበርበትን ጉድጓዱ ይምስ ጀ
ምሯል፡፡ይህም የሚያሳየው የአረመኔውና የበዝባዡ መደብ ጉ
ዱ ፍርጥርጥ ብሎ፣የተሰወረው ተገልጦ ቢታይበት ለመሸፈን
መቸከሩን ነው፡፡

መንግሥት በመሰለው ጊዜ ሁሉ የተማሪዎችን የተቀደሰ ተገባ
ርና እርቀ አስተዋይነት፣ለሕዝቡም የምናደርገውን ትግል ያ
ንቋሸሽል፡፡ዓላማችንንም ፍጹም የተበላሸ በማድረግ ከምንወ
ዳቸውና እንደራሰችን ከምናስበሳቸው አበትና እናት፣እህትና
ወንድሞቻችን አጧልቶ እኛን ለመጨረስ መዘጋጀቱ ለማንኛውም

ኢትዮጵያዊ ገልጸ ነው፡፡በዚህም መከረው የሆነ ያልሆነውን
የሚቓነና የማይታመነውን በመቀባጠር የእኛን አልቲት የኢት
ዮጵያ ሕዝብ እንዲደገፈው መጣሩ የሚዘነጋ አይደለም፡፡በየ
ጊዜው የሚሠራሠው ከዕውነት የራቀ ውንዛ ሁሉ ለጆሮ የሰለ
ቸና ፍጹም ቅጥ ያጣ ልፈፋ መሆኑን በሚ ሁሉ ተገነዘቦታል
አዳማጭና ተቀባይ ያጣ ልፈፋ በራስ ላይ ጥፋት የሚያስከት
ል መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ይህ መቅበዝበዝም አይበዛ
በትም፣"ቢሞቱ ያጣጥረሉና" አቀዳቸው በፕሮፓጋንዳ ብቻ አ
ላበቃም፡፡በአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ፕላን አርቃቂነት የ
ገፍ ሥራውን በንጹሕ ኢትዮጵያውያን ልጆች ላይ ለመፈጸም
ታጥቀው ተነሱ፡፡ፕላኑም መጀመሪያ ለተበዝባዡ ለኢትዮጵያ ሕ
ዝብ ደህንነት የሚጮሁትን ቆራጥ ተማሪዎች በጥር መቅጨት
ሆነ፡፡ከዚያም በኋላ በመንግሥቱ የተወሰዱት ተከታታይ "አ
ርምጃዎች" የአመጽና የሤራ ድርጊቶች መሆናቸው ገብቶን
አምበዛም በንደነቅና በንሸበር ቆየን፡፡

ግን ጠላታችን በዚህ አልተቆጠበም፡፡ይኸንኑ አረመኔያዊ
አድራጉቱን ለመፈጸም ሊባ የሁከት ማስነሻ ዘዴ መፈለግ ነ
ዉ ስለሆነበት ለተበዝባዡ ክፍል ተቆርቋሪ የነበረውን መሪ
ያችንን መግደል ሆነ፡፡እንግዲህ የጥላሁን ገዛው መገደል
የሚያስየን በጋዜጦች፣በራዲዮና በቴሌቪዥኖቻቸው ቢለፍፉ የ
ቆየው "አባብን በአንቁው" የሚለው አስተባሳብ በሥራ ላይ
መዋሉን ነው፡፡

ታህሣሥ 20 ቀን 1962 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የሚገኙ
የዩኒቨርሲቲ፣የሁለተኛ፣የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችና የሙያ
ቤተሰቦች ተገኝተው በግፍ የተገደለውን መሪያቸውንና ልጃቸ
ውን ለመቅበር በመዘጋጀት ላይ እንደነበሩ ከፖሊስና ከክቡ
ር ዘበኛ በተመለመሉ ወታደሮች አማካይነት "የገደሉትን አ
ሬብ ለመማረክ" ስለፈለጉ፣ለመቅበር ተሰብስበው በነበሩት
የሙያ ቤተዘመዶችና ተማሪዎች ላይ ተኩስ ከፍተው ከሃያ



ሰባት በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ገድለው ከመቶ አምሳ ሰባት
በማያንሱ ተማሪዎች ላይ ከባድ የመቁሰል አደጋ አደረሱ፡፡
በዶ አጁን ተሰልፎ በነበረ ተማሪ ላይ ተኩስ ከፍቶ ይኸን
ያህል አልቲት ማዳረስ ፋሽስት ጣሊያን የካቲት 12 ቀን
በኢትዮጵያውያን ላይ ከደረሰው ፍጅት የባሰ እንጂ ያነሰ
አይደለም፡፡ፖሊሱ የዱሃ ጠባቂ መሆኑ ቀርቶ የቀማር ጋሸ
ዣገሬ ሆኖ መቅረቱ ቢያስዝነን በቅርቡ ከክቡር ዘበኛ የተ
መለመሉትም ወታደሮች ከሰብአዊ ርህራሔ የራቀ ድርጊት መፈ
ጸማቸው ዓላማቸውን የባቱ መሆኑን ያሰያል፡፡"በአባቱ ከተ
ማ ልጅ ተቀማ" እንደተባለው ኢትዮጵያውያን ከወራሪው ኢጣ
ሊያን እና በወጧት አገራቸው ላይ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊስ
ቶችና በጥቂት ኢትዮጵያውያን በዝባዥ ቡችሎቻቸው በተቀጠሩ
ወታደሮች የልጆቻቸው ደም ያለ አገባብ ፈሰሰ፡፡

መንግሥቱ ከዚህ ቀደም የፈጸማቸውንና ለመፈጸም ያቀዳቸውን
አስቃቂ ድርጊቶች በመቃወም የሚከተሉትን ጥያቄዎች አናቀር
ባለን፡፡

<u>ጥያቄዎቻችን</u>

1 በበዝባዡ መደብ ተልከው ጥላሁን ገዛውን የገደሉት
ሰዎች ተይዘው ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ፡፡በዝባዡ መደ
ብ የጥላሁንን መገደል ከራሱ ለማውረድ ቀደም ብሎ
ሊያጠፋቸው ያሰበውን አንዳንዱ ተማሪዎችን በዚሁ ጉ
ዳይ መወንጀሉ ተቀባይነት የለውም፡፡

2 በታህሣሥ 20 ቀንና በተከታዮቹም ቀናት በአዲስ አ
በባና በየጠቅላይ ግዛቱ በሚገኙት ተማሪዎች ላይ ለ
ተደረገው አልቲት በሀላፊነት የሚጠየቁት የፖሊስና
የክቡር ዘበኛ አዛዦች ፍርድ ቤት ቀርበው አስፈላጊ
ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ፡፡

3 ለሞቱት ወንድሞቻችን ቤተሰቦች ተገቢው የነፍስ ዋጋ

እንዲከፈላቸውና ለደረሰባቸውም ታላቅ በደል መንግሥት በረዲዮና በጋዜጣ ይቅርታ እንዲጠይቃቸው።

4 ሀ. በፖሊስ ሠራዊት ሆስፒታል ያሉት የቆሰሉ ወንዶቻችን በዚህ ሆስፒታል የሚደረግባቸው በደል ከፍ ያለ ስለሆነ ወደሌላ ሆስፒታል እንዲዛወሩ።

ለ. ከምኒልክና ከሌሎችም ሆስፒታሎች በደንብ ባይድኑ የተባረሩት ቁስለኞች እንደገና ተመልሰው አስፈላጊው ሕክምና እንዲደረግላቸው

5 በየሰበብ አስባቡ በየእሥር ቤቱ የሚማቀቁት ተማሪዎች ያለአንዳች ማመንታት እንዲለቀቁ

6 በየቦታው የሚታደኑት ተማሪዎች በሴራዊ መብታቸው እንዲጠበቁ

7 የዩኒቨርሲቲ መተዳደሪያ ሕግ እንዲሻሻልና እንዲከበር። መንግሥት በመሰለው ጊዜ ሁሉ ወታደር ወደ ዩኒቨርሲቲው ግቢ መላኩን ያቁም።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጥያቄዎቻችን ፍጻሜ ካላገኙ ፍንክች የማንል መሆናችንን ማወቅ የገዢው መደብ ፈንታ ነው። የነጻ ኢትዮጵያዊያን ደም ፈሶ በከንቱ አይቀርም። ያስተዳደር መሠረት ስምምነት እንጂ ኃይልና ደም ማፍሰስ አይደለም። ኃይልና ጭካኔ በራስ ላይ ጥፋትን እንደሚያስከትል መረዳት ይጠቅማል። በኃይልና በደም ማፍሰስ የሚያምኑ ሁሉ ተንኮታኩተው መውደቃቸውን ታሪክ ያስረዳል። አባትና ልጅን አጣልቶ የገዛት ዘመን ማራዘሙ ፍቺ ያጣ ሕልም ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ደረጃው ይሻሻል፣ ትምህርት ይስፋፋ፣ መሬት ላራሹ የሚሉትና የመሰበሱት የተማሪዎች ቀና ዓላማዎች ቺም በሆኑ አስደጥረው በመቸ ጊዜ እልቂትን ካስከተሉ ሀዘኑ የተበዝባዡ መደብ ሁሉ ነው።



ለመሆኑ ለድሃና ለተበዘበዘው ሕዝብ ማሰብና መቆርቆር ወንጀል ነውን? በእኛ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ላይ የደረሰብንን እልቂትና መከራ ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ — የተበዝባዡ መደብ — አትኩሮ በመመልከት ላይ ነው። ጊዜ በመቸው ሰዓትም ጦሩን አንስቶ፣ ጠብመንጃውን አንግቶ የውስጣዊ ጠላቶቹን እንደሚደቁም የታወቀ ነው። የተበዘበዘ፣ የተጨቆነ፣ የተነጠቀ፣ የተራቆተ፣ የተናቀ፣ የተሰደበና የተዋረደ ሕዝብ ቢነሳ ጠላቱን ሳያንበረክክ ፊቱን እንደማያጥፍ በይታለም የተፈታ ነው። እንደሚታወቀው ሁሉ ዕውነት ትመነምናለች እንጂ አትጠፋም፣ ዕውነትን መከታ አድርገን ስለሆነ የምንሞተው ቢዘገይም እንኳን አሸናፊነት በእኛው እጅ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እጁን በዚህ በዝባዥ ክፍል ላይ እስኪሰነዝር ድረስ በቆራጥነት አቤቱታችንንና ጩኸታችንን እንቀጥላለን። ሀብት፣ ብልጽግና፣ ዕውቀት የእኩልነት መብት በኢትዮጵያ ይስፋፋ፣ ድህነት፣ ረሃብ፣ ድንቁርና፣ የሰው አገልጋይነት ይጥፉ ይላሉ <u>የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአንድ ድምጽ።</u>

እኛ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፣ የዩኒቨርሲቲ የብሔራዊ አገልግሎት ተማሪዎች፣ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ ከላይ የተመለከቱት ጥያቄዎች እስከአሥራ አምስት ቀን ድረስ ባይፈጸሙ ትምህርታችንንና ሥራችንን የማንቀጥል መሆናችንን እንዲታወቅልን።

## 2 የዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኅበር ለአድሃሪው መንግሥት ያቀረበው ጥያቄ

የዩኒቨርሲቲው መሁራን በማኅበራቸው አማካይነት ለፊውዳሉ መንግሥት ያቀረቡትን ጥያቄ ከዚህ በታች እንዳለ ስናሰፍር ረብቻቸው የሚያውቁትን ቁም ነገር እያስታወስን ነው::

"መንግሥቱ በመጠየቅ ብቻ የሚመለስ አይደለም::ያ ኗኑ መበስበስ ጀርሙን ያዳነቀረው ሥርዓተ መንግሥት ጥያቄዎችን ለመስማት ችሎታም ሆነ ፍላጎት የለውም::የሚገባው ቋንቋ የተያውቀ ትግል ብቻ ነው::ምሁራን ይህን መሠረታዊ ነገር እንዳልዘነጉት ስናምን በቅርቡም በታጋይ ወንድሞቻቸውና በረቮሉሽናዊ ተማሪዎቻቸው ጎን በመሰለፍ በጠቅላላው ለሰው ልጅ መብት፣ለዲሞክራሲ፣ለፍትህ፣ለብሔራዊ ነፃነት በበለጠ እንደሚታገሉ ያለመጠራጠር ነው::

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና በመንግሥቱ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ከጊዜ ወደጊዜ እየከረረ በመሔዱ መልኩን፣መንፈሱን፣ለውጦ ታኅሣሥ 20 ቀን 1962 ዓ.ም. የተፈጸመውም አሰቃቂና አሳዛኝ ሁኔታ አስከትሏል::በነዚህ ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያዊያን የዩኒቨርሲቲ መምህራን ትምህርት እንዳይቋረጥ የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ አድርገዋል::

በተለይም በዚሁ ዓመት መጀመሪያ አምና የተፈጠረው ሁከት ባስከተለው የትምህርት መጓደል ምክንያት የዩኒቨርሲቲው የትምህርት ፕሮግራም እንዳይሰናከል፣ጠብ እንዲበርድና ተማሪዎችም በተወሰነላቸው ጊዜ ውስጥ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ መምህራን ያደረጉት ከፍተኛ ጥረትና ድካም የሚዘነጋ አይደለም::



ይህንኑም ዓላማ መሠረት በማድረግ በዩኒቨርሲቲው ትምህርት እንዳይጓደልና የዩኒቨርሲቲው መሠረታዊ ዓላማ የሆነው የአካዳሚክ ነፃነት እንደበፍን ጥረት በማድረግ ላይ ሳለን፣ በመካከሉ ታኅሣሥ 20 ቀን 1962 ዓ.ም. የተፈጸመው አድራጎት ዩኒቨርሲቲው ተገቢና ትክክለኛ የሆነውን ተግባሩን ያለሥጋት ለመፈጸም የማይችል መሆኑን እምነት አሳድሮብናል

በዚሁ ቀን የየክብር ዘበኛ ባልደረቦች ከዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ገብተው ዓላማቸውን ለመፈጸም ሌላ ተመጣጣኝ ዘዴ ሳይፈልጉ የቀረበውን በበንሻ፣የራቀውን በጥይት ያለማቋረጥ ባደረጉት ተግባር ተማሪዎች ሲሞቱ በጨማሪም በተማሪዎችና በአስተማሪዎች ላይ የመቁሰል አደጋ አስከትሏል:: ባለፈው ዓመት የፖሊስ ባልደረቦች አራት ኪሎ ባለው የዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ገብተው ብዙ ተማሪዎችን አሥረው ወደሰንዳፋ በሚወስዱበት ጊዜ በአንድ ተማሪ ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ምክንያት ለጃንሆይ በቀረበው አቤቱታ፣ለዩኒቨርሲቲው መምህራን ወደፊት እንዲህ ያለ ሁናቴ እንደማይደረግ ከግርማዊነታቸው ንጉሣዊ ቃል ተሰጥቶ ነበር::ባለፈው ሰኞ ታኅሣሥ 20 ቀን ግን ይህው ንጉሣዊ ቃል ተደምስሶ ወታደሮች ከዩኒቨርሲቲው ግቢ ገቡ::ተማሪዎች ሞቱ፣ቆሰሉ፣በመምህራኑም ላይ የመቁሰል፣የመጉሳሳትና የመቀረፉ በደል ተፈጸመባቸው::ይህ ተደጋግሞ በዩኒቨርሲቲው ላይ የደረሰው ሁኔታ በዩኒቨርሲቲው መማርና ማስተማር ለሕይወት አስጊ መሆኑን አረጋግጦልናል::

እነዚህንና ይህንንም የመሰሰሉትን ሁኔታዎች በማመዛዘን ኢትዮጵያዊያን የዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኅበር የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፏል::

1 ማናቸውም የፖሊስ ሠራዊትም ሆነ ወይም ሌላ የጦር ኃይል ያለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ፈቃድ በዩኒቨርሲ

ነው ቀጥር ገቢ እንዲገበና በፕሬዚዳንቱም ፊታዩ
ከገበ ፕሬዚዳንቱና የመምህራኑ ተወካዮች በይወሰኑ
ት ዓናቸውም እርምጃ እንዲይወሰዱ በሚል መገፈስ የ
ዩኒቨርሲቲው ጀርብር ተሸሽሎ ለመማርና ለማስተማር
የሕይወት ዋስትና እንዲሰጥ ከልተደረገ

2 መተኪስና ማቁሰል ወቀሰሰውን ተመጻኛ በልሆነ ጋዜ
ሏ መጠየም ቢይገበቸው ታህሣሥ 20 ቀን ለተፈጸመው
ተገበር ኃዳፊ የሆኑት የክቡር ዘበኛ ባልደረቦች ጉ
ዓይ ተገርቶ በሕግ ፊት እንዲቀርቡ ከልተደረገ

3 በተጨማሪ ጃሰሕገ የታሥሩት ተማሪዎች እንዲለቀቁ ከ
ልተደረገ

የማስተማር ተገባሬችንን ለመፈጸም አንችልም፡፡

---

3 የፈሸት መንግሥት ታህሣሥ 20 ቀን በተማሪዎች ላይ ያ
ወረደው የቀይት ዘናብ ያንገሸገሸው የቤዝ ነስ ክልጅ ዷ
ን፤L. X. Tarpey ለመምህራን በልደረቦቻቸውና ለሕዝብ
የበተኑትን ጽሑፍ የቀለን እናሰፍራለን፡፡ Mr. Tarpey
በ24 ሰዓት ውስጥ አገሪቱን እንዲለቀ ተደርገዋል፡፡

On Decmber 29,1966, the campus was invaded by armed troops.Without just cause they murdered,beat and stabbed many students and staf.

I consider these acts of violence and brutality to be serious crimes against humanity and must be openly condemned.



There are many members of our academic community who share my viewpoint,but unfortunately will choose to remain silent. They are persons whose lives are guided by the principles of expediency and compromise. These lives are the people who can always find a convenient excuse to justify silence in the face of evil.These are the same types of individuals who sat quietly by while Hitler and his gang murdered some 6 million Jews.These people have no shame because they have no honour.

There is an Ethiopian proverb which says, "when the heart overflows it comes out through the mouth".As a faculty member,as an officer of the Univercity and as a human being,I cannot remain silent about these acts of murder and brutality.To do so would be to condone such actions.It would be a form of complicity and I would become a partner in the crime,a "respectable murderer".

---

My HSIU contract(Sec. I, para. 5, part d) says I must not use my position at the University to promote political or religious views. One interpretation of this clause is that I keep silent on any matter slightly related to politics or relgion.A more reasonable interpretation however, says that a faculty member must not use his classroom or official position as a pulpit for the dessemination of personal,political or religious views. This clause is not designed to repress free speech or to make us moral eunuchs.

## ለ. በአሜሪካ የተከናወኑት የማጋለጫ ትግሎች

1. ዲሴምበር 31፣1969 ዓ.ም. 50 የሚሆኑ ኢትዮጵያዊ
ያን በርከት ካሉ አፍሪካዊያንና አፍሮአሜሪካዊያን፣ፋር
ሲዊያንና ወደፊት ተራማጅ የአሜሪካን ተማሪዎች ጋር ሆ
ነው በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ ባለው የአድሃሪው የ
ኢትዮጵያ መንግሥት ኤምባሲና የአሜሪካን ኤምባሲ ፊት
ለፊት በሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ።መግቢያው በብዙ ፖሊሶች
ታጥሮ ነበር።

2 ጃንዋሪ 3፣1970 በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የሚገኙ የኢ
ትዮጵያ ተማሪዎች ታሬዛ ተሸክመው ከአንዱ የጥቁር በ
ተ ክርስቲያን ተነስተው እስከ ፊውዳሉ መንግሥት ኤም
ባሲ ድረስ ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ።

3 ጃንዋሪ 2፣1970 በካናዳ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ተማ
ሪዎች በኦታዋ በሚገኘው የፋሽስቱ የኢትዮጵያ መንግሥት
ኤምባሲ ፊት ለፊት የተቃውሞ ሰልፍ አደረጉ።የኤምባሲ
ው ሠራተኞች ሥራ አልገቡም ነበር።

## ሐ. በአውሮፓ የተደረጉት የማጋለጫ ትግሎች

1 ታህሣሥ 21 ቀን 1962 ዓ.ም. በሶቪየት ኅብረት
የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች የአድሃሪውን የኢትዮ
ጵያ መንግሥት ኤምባሲ ነፃ አውጥተው በውስጡ የሚገኘ
ውን የፕሮፓጋንዳ የመመጻደቂያ ስዕሎች ሁሉ ከቀዳደዱ
ና ከሰባበሩ በኋላ በየግድግዳው ላይ ሬቮሉሽናዊ ም
ንባብ" የሰፈረባቸው ሰሌዳዎችን ሰቀሉ — ለጠፉ። ነ
ፃ በወጣው ኤምባሲ ቅጥር ግቢ ውስጥ ታሬዛ የሚመስል
"ሳጥን ይዘው እየዞሩ መዝሙር በመዘመርና መግለጫ በ



መስጠት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገኝበትን አበያዊ ሁኔታ
እዚያ ለተሰበሰቡት ጋዜጠኞችና በአቅራቢያው ለተገኘው
ሕዝብ አስረዱ።

2 ታህሣሥ 27 ቀን 1962 ዓ.ም. በፓሪስ የሚገኙ የ
ኢትዮጵያ ተማሪዎች በፖሊስ የተከበበውን የኃይለሥላሴ
ንና የተከታዮችን ኤምባሲ ጥሰው ገብተው ኤምባሲውን
ለአኩል ሰዓት ያህል ነፃ በማውጣት ከውስጡ ከሚገኙት
የፕሮፓጋንዳ ጽሑፎችና ስእሎች አብዛኛውን "ለማጥፋት
ችለዋል።

በሌሎች የፈረንሣይ ከተማዎች የሚገኙ ተማሪዎች ደግሞ
ከሌሎች ወደፊት ተራማጅ ድርጅቶች ጋር በመቀላቀል የ
ተቃውሞ ድምጻቸውን አሰምተዋል።

የፈረንሣይ ተማሪዎች ብሔራዊ ማኅበር፣በፈረንሣይ የኢ
ትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የሰጠውን ማሳሰቢያ በመመር
ኮዝ፣ለፋሽስቱ የኢትዮጵያ መንግሥት "የኩነና" ቴሌግ
ራም ቢልክ ለፈረንሳይ ሕዝብ ደግሞ የአልቲቱን ሁኔቴ
ና የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግርና ስቃይ የሚገልጽ ጽሑፍ
በትነዋል።

3 ጥር 25 ቀን 1962 ዓ.ም. በስዊድን የሚገኙት
የኢትዮጵያ ተማሪዎች በስቶክሆልም የሚገኘውን የፋሽ
ስቱን የኢትዮጵያ መንግሥት ኤምባሲ ለ6 ሰዓት ያህ
ል ነፃ ከወጡ በኋላ በውስጡ የነበረውን የፕሮፓጋን
ዳና የመመጻደቂያ ዕቃ — ጽሑፍ፣ስእል፣ፍቶግራፍ —
አንዱ ባንዱ እየለተመ አውድመው ነፃ በወጣው ኤምባ
ሲ ግድግዳ ላይ የተቃውሞ ድምጻቸውን የሚያሰሙ ጽሑ
ፎችንና የኢትዮጵያን ትክክለኛ መልክ የሚያሳዩ ፎቶ
ግራፎችን ለጥፈዋል፣ሰቅለዋል።

ኤምባሲውን ነፃ ከማውጣታቸው በፊት ትንሽ ቀደም ብ

ለው ለስዊድን ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስ
ትር ለምን ኤምባሲውን ነፃ ለማውጣት እንደተገደዱ የ
ሚገልጽና ከአድኃሪው የኃይለሥላሴ መንግሥት ጋር ያላ
ቸውን ግንኙነት እንዲያቋርጡ የሚጠይቅ ቴሌግራም በኢ
ትዮጵያ ሕዝብ ስም ሲልኩ ኤምባሲው ውስጥ እንደገቡ
ለደረሱ ጋዜጠኞች ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር፣የ
ኢትዮጵያን አሰቃቂ ሁኔታ በዝርዝር ለማስረዳት ችለ
ዋል፡፡

4 የዴንማርክ ንጉሥ፣አሥረኛው ፍሬዴሪክ፣ኢትዮጵያን ለመ
ጎብኘትና የፊውዳሉን መንግሥት መሪዎች ለመገናኘት ጥ
ር 1 ቀን 1962 ከዴንማርክ መነሣቱ ይታወሳል፡፡በ
ዚሁ ቀን በዴንማርክ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች
ከሌሎች ወደፊት ተራማጅ ድርጅቶች ጋር ሆነው ይኸን
ኑ ጉዞ በመቃወም በኮፐንሀገን በሰላማዊ ሰልፍ አደርገዋ
ል፡፡

ለንጉሡ የሰጡት የመቃወሚያ ጽሑፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ
የሚደርስበትን ስቃይ በጥሬ ከዘረዘረና የታህሣሡን አ
ልቲት ካዘከረ በኋላ "ሰሞኑን እንደጎርፍ የወረደው
የኢትዮጵያ ወጣቶች ደም ገና አልደረቀም፡፡እጃቸው በ
ደም የተበከለውን የፋሽስት መንግሥት መሪዎች በአሁኑ
ሰዓት ሄዶ መጎብኘት ዲሞክራሲን በአንደበት ሳይሆን
በተግባር ጭምር ከተቀበሉ ሰዎች ድርጊት የራቀ ከመሆ
ኑም በላይ የነዚህን ነፍሰ ገዳዮች የአመጽ ሥራ ጭም
ር መደገፍ ስለሆነ ይህንን ጉዞህን በኃይል እንቃወመ
ቃለን" ሲል ይደመድማል፡፡

5 በሌሎች የአውሮፓ ክፍሎች የኢት. ተማሪዎች ለፋሽስቱ
የኢትዮጵያ መንግሥት የተቃውሞ ድምፃቸውን የሚያሰሙ፣
ለግንበር ቀደሞች የኢት. ተማሪዎች ድጋፋቸውንና ንዴ



ታቸውን የሚገልጹ ደብዳቤዎች ወይም ቴሌግራሞች ልከ
ዋል፡፡

<u>ማስታወሻ</u>

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ድርጊቶች የተፈጸሙት በተጨቆነው
ና በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ነው፡፡ከሥራ ላይ የዋሉ
ት ደግሞ በየቦታው በሚገኙት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራ
ት መሪነት ሲሆን፣ማኅበራት ሁሉ በያሉበት የተቻላቸውን የ
ማጋለጫ አርምጃ እንዲወስዱ መምሪያ የተሰጠው ከአውሮፓ የ
ኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ነው፡፡

---

መ. THE STUDENTS' SOCIETY OF McGILL UNIVERSI-
TY ለፊውዳሉ የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት መሪ የላከ
ውን "የኩነና" ቴሌግራምና ለግንበር ቀደሙ የኢትዮጵያ
ተማሪዎች ማኅበር ያስተላለፈውን የድጋፍ ቴሌግራም ለአ
ንባቢዎች እናቀርባለን፡፡

The Ethiopian Students Union in Europe

Dear Sirs:

Following are the texts of two telegrams which the Students' of McGill University has despatched to Addis Abeba

To: H.R.H. The Emperorof Ethiopia, Addis
Abeba, Ethiopia:

"We are surprised and grieved to learn that Ethiopia,the country which was perhaps the first to suffer from fascism has adopted fascist methods and ideas as its own. The murder of the President of the Students' Council and of other students by your régim on December 29 is an act history will not easily forget. We wish to voice our vociferous and indignant protest."

---

To: The Ethiopian Students' Union
P.O.Box 1776, Addis Abeba, Ethiopia

"Dear friends: Permit us to voice our grief, anger and sympathy stemming from the murder of the President of your Students' Union and of other students by the oppressive regim. The struggle against all forms of fascism must continue, and we want to express our solidarity with your struggle in Ethiopia.

signed
Julius Grey
President
Students' Society of
McGill University.



ROGERS & HAILE SELASSIE IN ADDIS ABABA
*A major role with a minor investment.*

ስእሉ የሚያሳየው ሮጀርስ፤የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አፈ-ቀላጤ በ
መሆን፤ጥገኞቹን ለመጐብኘትና እንዲከተሉ የሚጠበቅባቸውን ፖሊሲ
ለማስተላለፍ ባለፈው ፌብርዋሪ አፍሪካን በዞረበት ጊዜ ኢትዮጵያ ሲ
ደርስ የአድሃሪው ን ስርአተ·መንግስት መሪዎች መሪ ሲያስግድ